❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄

፩ አኰቴተ ቍርባን ዘአበዊነ ሐዋርያት በረከተ ጸሎቶሙ የሀሉ ምስለ ኵልነ ሕዝበ ክርስቲያን ለዓለመ ዓለም አሜን ።

፪ ይ.ካ. እግዚአብሔር ምስለ ኵልክሙ።

ይ. ሕ. ምስለ መንፈስከ ።

፫ ይ. ካ. አእኵትዎ ለአምላክነ ።

ይ. ሕ. ርቱዕ ይደሉ ።

ይ. ካ. አልዕሉ አልባቢክሙ ።

ይ.ሕ. ብነ ኀበ እግዚአብሔር አምላክነ ።

፬ ይ. ካ. ንአኵተከ እግዚኦ በፍቁር ወልድከ እግዚእነ ኢየሱስ ዘበደኃሪ መዋዕል ፈኖከ ለነ ወልደከ መድኀነ ወመቤዝወ መልአከ ምክርከ ።

፭ ዝ ቃል እንተ እምኔከ ውእቱ ወቦቱ ኵሎ ገበርከ በፈቃድከ ።

፮ ይ. ዲ. በእንተ ብፁዕ ወቅዱስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት አባ እገሌ ወብፁዕ ሊቀ ጳጳስነ አባ እገሌ እንዘ የአኵቱከ በጸሎቶሙ ወበስእለቶሙ እስጢፋኖስ ቀዳሚ ሰማዕት ዘካርያስ ካህን ወዮሐንስ መጥምቅ ።

❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄❄

፩ የአባቶቻችን የሐዋርያት የቍርባን ምስጋና ። የጸሎታቸው በረከት በሁላችን ይደር ለዘላለሙ አሜን ።

፪ ይ. ካ. እግዚአብሔር ከሁላችሁ ጋራ ይሁን ።

ይ. ሕ. ከመንፈስህ ጋራ ።

፫ ይ. ካ. አምላካችንን አመስግኑት ።

ይ. ሕ. እውነት ነው ይገባል ።

ይ. ካ. ልቡናችሁን ከፍ ከፍ አድርጉ።

ይ. ሕ. በአምላካችን በእግዚአብሔር ዘንድ አለን ።

፬ ይ. ካ. አቤቱ በተወደደ ልጅህ በጌታችን በኢየሱስ እናመሰግን ሃለን ። በኋለኛው ዘመን የምክርህን አበጋዝ መድኃኒትና ቤዛ የሚሆን ልጅህን የሰደድህልን ።

፭ ይህ ቃል ካንተ የተገኘ ነው በር ሱም ሁሉን በፈቃድህ አደረግህ ።

፮ ይ. ዲ. ብፁዕ ቅዱስ ስለሚሆን ስለ ሊቀ ጳጳሳቱ ስለ አባ እገሌ ። ብፁዕም ስለሚሆን ስለ አባ እገሌ። በጸሎታቸውና በልመናቸው ሲያመሰግኑህ የሰማዕታት መጀመሪያ እስጢፋኖስ ። ካህኑ ዘካርያስና መጥምቁ ዮሐንስ ።

www.ethiopianorthodox.org

፺ ወበእንተ ኵሎሙ ቅዱሳን ወሰማዕት
እለ አዕረፉ በርትዕት ሃይማኖት

፱ ፱ ማቴዎስ ወማርቆስ ሉቃስ ወዮ
ሐንስ ፬ቱ ወንጌላውያን ማርያም
ወላዲተ አምላክ ስምዖን ጴጥሮስ
ወእንድርያስ ያዕቆብ ወዮሐንስ
ፊልጶስ ወበርተሎሜዎስ ቶማስ
ወማቴዎስ ታዴዎስ ወናትናኤል
ወያዕቆብ ወልደ እልፍዮስ ወማት

፫ ፫ ያስ ፲ወ፪ቱ ሐዋርትያት ወያዕቆብ
ሐዋርያ እኁሁ ለእግዚእነ ኤጲስ
፱ ቆጶስ ዘኢየሩሳሌም ጳውሎስ ወጢ
ሞቴዎስ

፱ ፱ ሲላስ ወበርናባስ

፫ ፫ ቲቶ ፊልሞና ወቀሌምንጦስ

፱ ፱ ፸ወ፪ቱ አርድእት ፫ቱ፻ ቢጽ
፫ቱ፻፲ወ፰ ርቱዓነ ሃይማኖት ጸሎተ
ኵሎሙ ይብጽሐነ ወምስሌሆሙ
ኪያነ ሐውጽ ።

፳ ወተዘከር እንተ ላዕለ ኵሉ ዘሐዋር
ያት ቤተ ክርስቲያን በሰላማ ወበ

፺ በቀናች ሃይማኖት ስላረፉ ስለ
ቅዱሳንና ሰማዕታት ሁሉ አራቱ
ወንጌላውያን ማቴዎስና ማርቆስ
ሉቃስና ዮሐንስ አምላክን የወለ
ደች ማርያም ጴጥሮስ የተባለ
ስምዖን እንድርያስም ያዕቆብና
ዮሐንስ ፊልጶስና በርተሎሜዎስ
ቶማስና ማቴዎስ ታዴዎስና ናትና
ኤል የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብ
ማትያስም ዐሥራ ሁለቱ ሐዋር
ያት የኢየሩሳሌም ኤጲስ ቆጶስ የጌ
ታችን ወንድም ሐዋርያ ያዕቆብ
ጳውሎስ ጢሞቴዎስ ሲላስና በርና
ባስ ቲቶ ፊልሞና ቀሌምንጦስም
ሰባ ሁለቱ አርድእት ፫፻ ባልንጀሮች
ሃይማኖታቸው የቀና ሦስት መቶ
አሥራ ስምንት ሊቃውንት የሁ
ሉም ጸሎት ትድረሰን ከእነሱም
ጋራ እኛን ጐብኝ ።

፳ ከሁሉ በላይ የምትሆን የሐዋርያት
ንም ቤት ክርስቲያን አስብ በፍቅር

www.ethiopianorthodox.org

ከቡር ደም እንተ በክርስቶስ ተገብረ ።

፱ ተዘከር ዘሎ ሊቃነ ጳጳሳት ጳጳሳት ኤጲስ ቆጶሳተ ቀሳውስተ ወዲያቆናተ እለ ያረትዑ ፍኖተ ቃል ዘበአማን ።

፲ ወይበል ንፍቅ ካህን ጸሎተ ቡራኬ ዘባስልዮስ ።

አ ሥሉስ ቅዱስ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ባርክ ዲበ ሕዝብከ ፍቁራን ክርስቶሳውያን በበረከተ ሰማያውያን ወምድራውያን ።

ቡራኬ ላዕለ ሕዝብ ።

ይባርክ ሠራዒ ካህን በበገጹ ለለይቤ ንፍቅ ባርክ ።

፲፩ ወፈኑ ላዕሌነ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ወረሲ ኆዋኆወ ቤተ ክርስቲያንከ ቅድስተ ርኅዋተ ለነ በምሕረት ወበአሚን ወፈጽም ለነ አሚነ ሥላሴከ ቅድስት እስከ ደኃሪት እስትንፋስ ።

፲፪ አ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ ሐውጽ ሕሙማነ ሕዝብከ ፈውሶሙ ወምርሐሙ ለአበዊነ ወለአኀዊነ እለ ሖሩ ወተአንገዱ ወሚጠሙ ኀበ ማኅደሪሆሙ በሰላም ወበጥዒና ።

ርኅዋ በክርስቶስም በተደረገው በከበረ ደም ።

፱ በእውነት የቃልን መንገድ የሚያቀኑ ሊቃነ ጳጳሳቱን ጳጳሳቱን ኤጲስ ቆጶሳቱን ቀሳውስቱንና ዲያቆናቱንም ሁሉ አስብ ።

፲ ንፍቅ ካህን ባስልዮስ የተናገረውን የቡራኬ ጸሎት ይበል ።

ልዩ ሦስት የምትሆን አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ሆይ የሚፋቀሩ የክርስቶስ ወገኖች የሚሆኑ ሕዝብህን በሰማያውያንና በምድራውያን በረከት ባርክ ።

ሕዝቡን ይባርክ ንፍቅ ቄስ ባርክ ባለው ቍጥር ሠራዒው ቄስ በየስልቱ ይባርክ ።

፲፩ በእኛ ላይም የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ ላክ የቅድስት ቤተ ክርስቲያንህንም ደጆች በምሕረትና በሃይማኖት እንዲከፈቱ አድርግልን ። እስከ መጨረሻዪቱ ሕቅታም ድረስ ልዩ ሦስትነትህን ማመንን ፈጽምልን ።

፲፪ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ የታመሙ ወገኖችህን ጐብኝ የሄዱትንና እንግዶች የሆኑትን አባቶቻችንን ወንድሞቻችንን መርተህ በሰላምና በጤና ወደ ቤታቸው መልሳቸው ።

www.ethiopianorthodox.org

፲፫ ባርክ ነፋሳተ ሰማይ ። ቡራኬ
መንገለ ሰማይ ።
ወዝናማተ ወፍሬያተ ምድር ዘዛቲ
ዓመት በከመ ጸጋከ ወረሲ ፍግዓ
ወተድላ ወትረ ዲበ ገጸ ለምድር
ቡራኬ ላዕለ ምድር ።

፲፬ ወአጽንዕ ለነ ሰላመከ ሚጥ ልበ
ነገሥት አዚዛን ለአሠንዮ ላዕሌነ
በኵሉ ጊዜ ።

፲፭ ጸጉ ሰላመ ለሊቃውንተ ቤተ
ክርስቲያን እለ ጉቡአን ውስተ
ቤተ ክርስቲያንከ ቅድስት ኵሎ
ጊዜ ለኵሉ ለለ፩ዱ በበአስማቲ
ሆሙ በቅድመ ነገሥት ኃያላን
አምላክነ አንጎ ሎሙ ።

፲፮ ወአዕርፍ ነፍሳተ አበዊነ ወአኀዊነ
ወአኀቲነ እለ ኖሙ ወአዕረፉ
በርትዕት ሃይማኖት ።

፲፯ ወባርክ ዲበ እለ ያስተነትኑ
ቡራኬ ላዕለ ሕዝብ ።
በዕጣን ወቍርባን ወወይን ወቅብዕ
ወዘይት ወመንጠዋልዕ ወመጻሕ
ፍተ ምንባባት ወንዋያተ ቤተ
መቅደስ ከመ ክርስቶስ አምላክነ
ይዕሥዮሙ በኢየሩሳሌም ሰማያ
ዊት ።

፲፰ ወለኵሎሙ እለ ተጋብኡ ምስሌነ
ይኅሥሡ ምሕረተ ክርስቶስ አም
ላክነ ተሣሃል ላዕሌሆሙ ወለኵ

፲፫ የሰማዩን ነፋስ ባርክ ። ወደ
ሰማይ ይባርክ ።
ዝናሙንም በዚህች ዓመት የሚያፈ
ራውን የምድሩን ፍሬ እንደ ቸርነ
ትህ ባርክ ዘወትር ተድላንና ደስ
ታን አድርግ ።
ወደ ምድር ይባርክ ።

፲፬ ሰላምህንም አጽናልን ሁልጊዜ
ለኛ በጎ ነገርን ሊያደርጉልን ጽኑ
ዓን የሚሆኑ የነገሥታቱን ልቡና
መልስ ።

፲፭ በቅድስት ቤተ ክርስቲያንህ ሁል
ጊዜ ለሚሰበሰቡ ለቤተ ክርስቲያን
ሊቃውንት ፍቅርን ስጥ ። ለሁሉም
ለያንዳንዱ በየስማቸው ኃያላን
በሚሆኑ በነገሥታቱ ፊት ሰላምን
አብዛላቸው ።

፲፮ አምላካችን ሆይ በቀናች ሃይማኖት
ሆነው ያንቀላፉትንና ያረፉትን
ያባቶቻችንንና የወንድሞቻችንን
የእኅቶቻችንንም ነፍስ አሳርፍ ።

፲፯ አምላካችን ክርስቶስ በኢየሩሳ
ሌም ሰማያዊት ዋጋቸውን ይከፍላ
ቸው ዘንድ ዕጣንና ቍርባን ወይ
ንና ሜሮን ዘይትም መጋረጃም
የንባብ መጻሕፍቶችን የቤተ መቅደ
ስንም ንዋያት በመስጠት የሚያገ
ለግሉትንም ባርክ ።
ሕዝቡን ይባርክ ።

፲፰ ይቅርታን ያገኙ ዘንድ ከእኛ ጋራ
የተሰበሰቡትንም ሁሉ አምላካችን
ክርስቶስ ሆይ ይቅር በላቸው ።

www.ethiopianorthodox.org

ሎሙ እለ አምጽኡ ምጽዋተ በቅድመ መንበርከ መፍርህ ወመንደግፅ ተወከፎሙ ።

፲፱ ወእንጌ ለኵላ ነፍስ ዕፅብት ወእለ እሡራን በመዋቅሕት ወእለ ሀለዉ ውስተ ስደት ወፂዋዌ ።

፳ ወእለ እኁዛን በቅኔ መሪር አምላክነ አድኅኖሙ በምሕረትከ ኦ ሊቅነ ኢየሱስ ክርስቶስ ለኵሎሙ እለ አዘዙነ ከመ ንዘክሮሙ በጊዜ አስተብቍዖትነ ኀቤከ ተዘከሮሙ በመንግሥትከ ሰማያዊት ወሊተኒ ለኃጥእ ገብርከ ተዘከረኒ ።

፳፩ ኦ እግዚኦ አድኅን ሕዝበከ ወባርክ ርስተከ ቡራኬ ላዕለ ሕዝብ ሪዓየሙ ወአልዕሎሙ እስከ ለዓለም ።

፳፪ ፪ ይ· ዲ· ንፍቅ መሐሮሙ እግዚኦ ወተሣሀሎሙ ለሊቃነ ጳጳሳት ጳጳሳት ኤጲስ ቆጶሳት ቀሳውስት ወዲያቆናት ወኵሎሙ ሕዝበ ክርስቲያን ።

፳፫ ይ· ካ· ለእሉኒ ወለኵሎሙ አዕርፍ ነፍሶሙ ወተሣሃሎሙ ዘፈኖከ እምሰማይ ወልደከ ውስተ ማኅፀነ ድንግል ተፀውረ በከርሥ ሥጋ ኮነ ወልደቱ ተዐውቀ እመንፈስ ቅዱስ

፳፬ ይ· ዲ· እለ ትነብሩ ተንሥኡ ።

፳፭ ይ· ካ· ለከ ለዘይቀውሙ ቅድሜከ እልፍ አእላፋት ወትእልፊተ አእ

በሚያስፈራና በሚያስደነግፅ በመንበርህ ፊት ምጽዋት ያመጡትንም ሁሉ ተቀበላቸው ።

፲፱ የተጨነቀችዪቱን ነፍስ ሁሉ አሳርፍ በሰንሰለት የታሠሩትን በስደትና በምርኮ ያሉትንም ።

፳ መሪር በሆነ አገዛዝ የተያዙትንም አምላካችን ሆይ በቸርነትህ አድናቸው ። መምህራችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ወዳንተ በምንማልድበት ጊዜ እንድናስባቸው ያዘዙንን ሁሉ በሰማያዊት መንግሥትህ አስባቸው ኃጥእ ባርያህን እኔንም አስበኝ ።

፳፩ አቤቱ ሕዝብህን አድን ርስትህንም ባርክ ። ሕዝቡን ይባርክ ። ጠብቃቸው እስከ ዘላለምም ከፍ ከፍ አድርጋቸው ።

፳፪ ይ· ዲ· ንፍቅ አቤቱ የጳጳሳቱን አለቆች ጳጳሳቱንና ኤጲስ ቆጶሳቱን ቀሳውስቱንና ዲያቆናቱን የክርስቲያንንም ወገኖች ሁሉ ማራቸው ይቅርም በላቸው ።

፳፫ ይ· ካ· የእሊህንም የሁሉንም ነፍሳቸውን አሳርፍ ይቅርም በላቸው ። ልጅህን ከሰማይ ወደ ድንግል ማኅፀን የሰደድኸው በማኅፀን ተወሰነ ሥጋም ሆነ መወለዱም በመንፈስ ቅዱስ ታወቀ ።

፳፬ ይ· ዲ· የተቀመጣችሁ ተነሡ ።

፳፭ ይ· ካ· አእላፈ አእላፋትና ትእልፊት አእላፋት የሚሆኑ ቅዱሳን

ላፉት ቅዱሳን መላእክት ወሊቃነ መላእክት ።

፷፮ ይ· ዲ· ውስተ ጽባሕ ነጽሩ ።

፷፯ ይ· ካ· ወክቡራን እንስሳ እለ ፯ቱ ክነፊሆሙ ሱራፌል ወኪሩቤል በ፪ኤ ክነፊሆሙ ይከድኑ ገጾሙ

፪ ወበ፪ኤ ክነፊሆሙ ይከድኑ እገሮሙ ወበ፪ኤ ክንፍ ይሠሩ እምጽንፍ ወእስከ አጽናፈ ዓለም ።

፷፰ ይ· ዲ ንነጽር ።

፷፱ ይ· ካ· ወዘልፈ እንከ ኲሎሙ ከመ ኪያከ ይቄድሱ ይዌድሱ ወምስለ

፪ ፪ ኲሎሙ እለ ይቄድሱከ ወይዌድሱከ ።

፸ ዓዲ ተወከፍ ዘዚአነሂ ቅዳሴ እለ

፪ ዘንብለከ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ፀባዖት ፍጹም ምሉእ ሰማያተ ወምድረ ቅድሳተ ስብሐቲከ ።

፸፩ ይ· ዲ· አውሥኡ ።

፸፪ ይ· ሕ· ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ጸባዖት ፍጹም ምሉእ ሰማያተ ወምድረ ቅድሳተ ስብሐቲከ ።

መላእክት የመላእክትም አለቆች ከፊትህ ለሚቆሙልህ ለአንተ ።

፷፮ ይ· ዲ· ወደ ምሥራቅ ተመልከቱ ።

ይ· ካ· ክንፋቸው ስድስት የሚሆን ክቡራን አርባዕቱ እንስሳ ሱራፌልና ኪሩቤልም ።

፷፯ በሁለት ክንፋቸው ፊታቸውን ይሸፍናሉ በሁለት ክንፋቸው እግራቸውን ይሸፍናሉ በሁለት ክንፋቸው ከዳርቻ እስከ ዓለም ዳርቻ ይወጣሉ ።

፷፰ ይ· ዲ· እናስተውል ።

፷፱ ይ· ካ· ሁሉም ዘወትር አንተን ከሚቀድሱህና ከሚያመሰግኑህ ሁሉ ጋራ እንዲቀድሱና እንዲያመሰግኑ ።

፸ ዳግመኛ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ፍጹም አሸናፊ እግዚአብሔር የጌትነትህ ምስጋና በሰማይና በምድር የመላ ነው የምንልህን የኛንም ምስጋና ተቀበል ።

፸፩ ይ· ዲ· ተሰጥዎውን መልሱ ።

፸፪ ይ· ሕ· ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ፍጹም አሸናፊ እግዚአብሔር የጌትነትህ ምስጋና በሰማይና በምድር የመላ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

፴፫ ይ· ካ· አሜን መልአ ሰማያት ወምድረ ቅድሳት ስብሐቲከ በእግዚእነ ወአምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ወልድከ
፱ መጽአ ወእምድንግል ተወልደ ከመ ፈቃደከ ይፈጽም ወሕዝበ ለከ ይግበር ።

፴፬ ይ· ሕ· ተዘከረነ እግዚኦ በውስተ መንግሥትከ ተዘከረነ እግዚኦ እሊቅነ ተዘከረነ እግዚኦ በውስተ መንግሥትከ በከመ ተዘከርኮ ለፈያታዊ ዘየማን እንዘ ሀሎከ ዲበ ዕፀ መስቀል ቅዱስ ።

፴፭ ወእምዝ ንፍቅ ካህን ይውግር ዕጣነ ወያቅርብ ሎቱ ማዕጠንተ ወይዕጥን እዴሁ ወያዕርግ በበ፫ቱ ጊዜ ላዕለ ኅብስት ወጽዋዕ ።

፴፮ ይ· ካ· ሰፍሐ እደዊሁ ለሕማም
፱ ሐመ ከመ ሕሙማነ ያድኅን እለ ተወከሉ በላዕሌከ ።

፴፯ ዘተውህበ በፈቃዱ ለሕማም ከመ
፲ ፲ ሞተ ይሥዓር ወማእሠረ ሰይጣን ይብትክ ወይኪድ ሲኦለ ቅዱሳነ ይምራሕ ሥርዓተ ይትክል ወትንሣኤሁ ያዐውቅ ።

፴፰ ይ· ዲ· አንሥኡ እደዊክሙ ቀሳውስት ።

፴፫ ይ· ካ· የጌትነትህ ምስጋና በጌታችን በአምላካችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በእውነት በሰማይና በምድር መላ ቅዱስ ልጅህ መጣ ከድንግልም ተወለደ ፈቃድህን ይፈጽም ዘንድ ሕዝቡንም ላንተ ያደርግ ዘንድ ።

፴፬ ይ· ሕ· አቤቱ በመንግሥትህ አስበን መምህራችን ሆይ አቤቱ አስበን ቅዱስ በሚሆን በዕፀ መስቀል ላይ ሳለህ ፈያታዊ ዘየማንን እንዳሰብከው አቤቱ በመንግሥትህ አስበን።

፴፭ ከዚህ በኋላ ንፍቅ ቄስ ዕጣኑን አግብቶ ማዕጠንቱን ያቅርብለት ። እጁንም አጥኖ ሦስት ጊዜ ከሥጋው ላይ ሦስት ጊዜ ከደሙ ላይ ያሳርግ ።

፴፮ ይ· ካ· እጆቹን ለሕማም ዘረጋ ። በርሱ ያመኑ ሕሙማንን ያድን ዘንድ ታመመ ።

፴፯ ሞትን ይሽር ዘንድ የሰይጣንንም ማሠሪያ ይቈርጥ ዘንድ ሲኦልንም ይረግጥ ዘንድ ቅዱሳንን ይመራ ዘንድ ሥርዓትን ይሠራ ዘንድ ትንሣኤውንም ይገልጽ ዘንድ በፈቃዱ ለሕማም ተሰጠ ።

፴፰ ይ· ዲ· ቀሳውስት እጃቻችሁን አንሡ ።

www.ethiopianorthodox.org

፴፱ ይ· ካ· በይእቲ ሌሊት እንተ ባቲ
አመ ያገብእዎ ነሥአ ኅብስተ
በእደዊሁ ቅዱሳት ወብፁዓት እለ
እንበለ ነውር ።

በዝየ ያንሥእ ኅብስተ ።

፵ ይ· ሕ· ነአምን ከመ ዝንቱ ውእቱ
በአማን ነአምን ።

፵፩ ይ· ካ· አንቃዕደወ ሰማየ ኀቤከ
ኀበ አቡሁ አእኰተ ባረከ ወፈተተ
ቡራኬ ላዕለ ኅብስት ፫ተ ጊዜ ።
ወእምዝ ያንቅዖ ለኅብስት ኀበ ፭ቱ
ገጽ ንስቲተ እንዘ ኢይሌልዮ ።

፵፪ ወወሀቦሙ ለአሊአሁ አርዳኢሁ
ወይቤሎሙ ንሥኡ ብልዑ ዝ
ኅብስት "እማሬ" ሥጋየ ውእቱ
ለዘበእንቲአክሙ ይትፌተት ለኅድ
ገተ ኃጢአት ።

፵፫ ይ·ሕ· አሜን አሜን አሜን ነአምን
፪ ወንትአመን ንሴብሐከ እ እግዚእነ
ወአምላክነ ዝንቱ ውእቱ በአማን
ነአምን ።

፵፬ ይ· ካ· ወከማሁ ጽዋዐኒ አእኰቶ
ባሪኮ ቡራኬ ላዕለ ጽዋዕ ፫ተ
ጊዜ ። ወቀዲሶ ወወሀቦሙ
ለአሊአሁ አርዳኢሁ ወይቤሎሙ
ንሥኡ ስትዩ ዝ ጽዋዕ "እማሬ"
ደምየ ውእቱ ዘለበእንቲአክሙ
ይትከዐው ለሥርየተ ኃጢአት ።

፴፱ ይ· ካ· እርሱን በያዙባት በዚያች
ሌሊት ነውር በሌለባቸው ንዑዳት
ክቡራት ብፁዓትም በሚሆኑ እጆቹ
ኅብስቱን አንሥቶ ያዘ ።

በዚህ ጊዜ ኅብስቱን ያንሣ ።

፵ ይ· ሕ· ይህ እንደ ሆነ በእውነት
እናምናለን ።

፵፩ ይ· ካ· ወደ አንተ ወደ አባቱ ወደ
ሰማይ ቀና ብሎ አመሰገነ ባረከ
ቈረሰ ። በኅብስቱ ላይ ፫ ጊዜ
ይባርክ ። ከዚያም በኋላ ኅብስቱን
ሳይለየው ከአምስት ላይ ጥቂት
ያንቃው ።

፵፪ ይ· ካ· ለወገኖቹ ለደቀ መዛሙርቱ
ሰጣቸው ። ንሡ ብሉ ይህ ኅብስት
"እማሬ" ለኃጢአት ማስተሥረያ
ሊሆን ስለ እናንተ የሚፈተት
ሥጋዬ ነው አላቸው ።

፵፫ ይ· ሕ· አሜን አሜን አሜን
እናምናለን እንታመናለንም ።
ጌታችንና አምላካችን ሆይ እናመ
ሰግንሃለን ይህ እርሱ እንደ ሆነ
በእውነት እናምናለን ።

፵፬ ይ· ካ· እንዲሁም ጽዋውን
አመስግኖ ባርኮ በጽዋው ላይ ፫
ጊዜ ይባርክ ።
አክብሮ ለወገኖቹ ለደቀ መዛሙርቱ
ሰጣቸው ንሡ ጠጡ ይህ ጽዋ
"እማሬ" ለኃጢአት ማሥተሥርያ
ሊሆን ስለ እናንተ የሚፈስ ደሜ
ነው አላቸው ።

www.ethiopianorthodox.org

በገዘየ ይነክነኮ ለጽዋዕ በትእምርተ መስቀል በእደዊሁ ዘየማን ።

፸፫ ይ· ሕ· አሜን አሜን አሜን ነአምን ወንትአመን ንሴብሐከ ኦ እግዚእን ወአምላክነ ዝንቱ ውእቱ በአማን ነአምን ።

፸፬ ይ· ካ· ወሶበ ትገብርዎ ለዝንቱ ተዝካረ ዚአየ ግበሩ ።

፸፭ ይ· ሕ· ንዜኑ ሞተከ እግዚኦ ወትንሣኤከ ቅድስተ ነአምን ዕርገተከ ወዳግመ ምጽአተከ ንሴብሐከ ወንትአመነከ ንስእለከ ወናስተብቍዐከ ኦ እግዚእን ወአምላክነ።

፸፮ ይ· ካ· ይእዜኒ እግዚኦ እንዘ ንዜከር ሞተከ ወትንሣኤከ ንትአመነከ ወናቀርብ ለከ ዘንተ ኅብስተ "እማሬ" ወዘንተ ጽዋዐ "እማሬ"

፸፯ እንዘ ነአኵተከ ወቦቱ ረሰይከ ለነ ለተድላ ንቁም ቅድሜከ ወለከ ንትከሀን ንስእለከ እግዚኦ ወናስተበቍዐከ ከመ ትፌኑ መንፈሰ ቅዱሰ ወኀይለ ዲበ ዝንቱ ኅብስት "እማሬ" ወላዕለ ዝ ጽዋዕ "እማሬ" ።

በዚህ ጊዜ ጽዋውን በቀኝ እጁ በአራቱ ማዕዘን ይወዘውዘው ።

፸፫ ይ· ሕ· አሜን አሜን አሜን እናምናለን እንታመናለንም ። ጌታችንና አምላካችን ሆይ እናመሰግንሃለን ይህ እርሱ እንደ ሆነ በእውነት እናምናለን ።

፸፬ ይ· ካ· ይህን በምታደርጉበት ጊዜም የኔን መታሰቢያ አድርጉ ።

፸፭ ይ· ሕ· አቤቱ ሞትህን ቅድስት ትንሣኤህንም እንነግራለን ። ዕርገትህን ዳግመኛም መምጣትህን እናምናለን እናመሰግናለን እናምንሃለንም ጌታችንና አምላካችን ሆይ እንለምንሃለን እንማልድሃለንም ።

፸፮ ይ· ካ· አሁንም አቤቱ ሞትህንና ትንሣኤህን እያሰብን እናምንሃለን እያመሰገንህ ይህን ኅብስት "እማሬ" ይህንም ጽዋ "እማሬ" እናቀርብልሃለን ። በፊትህ እንቆም ዘንድ አንተንም እናገለግል ዘንድ በርሱ ተድላን አደረግህልን አቤቱ እንለምንሃለን እንማልድሃለንም በዚህ "እማሬ" ኅብስት ላይ ቅዱስ መንፈስን ኃይልንም ታሳድር ዘንድ በዚህም "እማሬ" በጽዋው ላይ ።

www.ethiopianorthodox.org

፵፱ ፫ ፫ ይረስዮ ሥጋሁ ወደሞ ለእግዚእነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ለዓለመ ዓለም ።

ቡራኬ ላዕለ ኅብስት ፩ደ ጊዜ ወላዕለ ጽዋዕ ፩ደ ጊዜ ወላዕለ ፪ኤሆሙ ፩ደ ጊዜ ።

፶ ይ· ሕ· አሜን እግዚእ መሐረነ እግዚእ መሀከነ እግዚእ ተሣሃለነ።

፶፩ ይ· ዲ· በኵሉ ልብ ናስተብቍዕ ለእግዚአብሔር አምላክነ ኅብረተ መንፈስ ቅዱስ ሠናየ ከመ ይጸግወነ ።

፶፪ ይ· ሕ· በከመ ሀሎ ህልወ ወይሄሉ ለትውልደ ትውልድ ለዓለመ ዓለም።

በዝየ ይኅትም ሥጋ በደም ጠሚዖ በአፅባዕቱ ።

፶፫ ይ· ካ· ደሚረከ ተሀቦሙ ለኵሎሙ ለእለ ይነሥእዎ እምኔሁ ይኩኖሙ
፱ ለቅድሳት ወለምልአተ መንፈስ ቅዱስ ወለአፅንዖ ሃይማኖት ዘበአማን ከመ ኪያከ ይቄድሱ ወይዌድሱ ወለወልድከ ፍቁርከ ኢየሱስ ክርስቶስ ለዓለመ ዓለም ።

፶፬ ይ· ካ· ሀበነ ንኅበር በዘዚአከ መንፈስ ቅዱስ ወፈውሰነ በዝንቱ

፵፱ የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም ያደርገው ዘንድ ለዘላለሙ ።

አንድ ጊዜ ኅብስቱን አንድ ጊዜ ጽዋውን ይባርክ ። ሁለቱንም አንድ ጊዜ ይባርክ ።

፶ ይ· ሕ· አሜን አቤቱ ማረን አቤቱ ራራልን አቤቱ ይቅር በለን ።

፶፩ ይ· ዲ· በፍጹም ልብ አምላካችንን እግዚአብሔርን እንማልደው ያማረ የመንፈስ ቅዱስን አንድነት ይሰጠን ዘንድ ።

፶፪ ይ· ሕ· በፊት እንደ ነበረ ለዘላለሙ ለልጅ ልጅ ይኖራል ።

በዚህ ጊዜ በጣቱ ጠምቶ በደሙ ሥጋውን ይቅባ ።

፶፫ ይ· ካ· ከርሱ ለሚቀበሉ ሁሉ አንድ አድርገህ ለንጽሕና መንፈስ ቅዱስንም ለመመላት እውነተኛውንም ሃይማኖት ለማጽናት ስጣቸው አንተን ይቀድሱና ያመሰግኑ ዘንድ ልጅህን ወዳጅህን ኢየሱስ ክርስቶስንም ከመንፈስ ቅዱስ ጋራ ለዘላለሙ ።

፶፬ ይ· ካ· የአንተ በሚሆን በመንፈስ ቅዱስ አንድ እንሆን ዘንድ ስጠን

www.ethiopianorthodox.org

ጽርስፎራ ከመ ብከ ንሕየው ዘለኩሉ ዓለም ወለዓለመ ዓለም ።

ይ· ሕ· ከማሁ ።

፺፭ ይ· ካ· ቡሩክ ስሙ ለእግዚአብሔር ወቡሩክ ዘይመጽእ በስመ እግዚአብሔር ወይትባረክ ስመ ስብሐቲሁ ለይኩን ለይኩን ቡሩክ ለይኩን ።

ይ· ሕ· ከማሁ ።

፺፮ ይ· ካ· ፈኑ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ላዕሌነ ።

ይ· ሕ· ከማሁ ።

፺፯ ይ· ዲ· ተንሥኡ ለጸሎት ።

ይ· ሕ· እግዚኦ ተሣሃለነ ።

ይ· ካ· ሰላም ለኵልክሙ ።

ይ· ሕ· ምስለ መንፈስከ ።

፺፰ ይ· ካ· ጸሎተ ፈትቶ ።

ወካዕበ ናስተበቍዖ ዘኵሎ ይእኅዝ እግዚአብሔር አብ ለእግዚእ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ።

፺፱ ከመ የሀበነ በበረከት ንንሣእ ዘእምቅዱስ ምሥጢር ጽንዓተ ለነ የሀ

፪ በነ ወኢመንሂ እምውስቴትነ ኢያ

፪ ርስሕ አላ ለኵሉ ተድላሆሙ ይረሲ

ለእለ ይትሜጠዉ ንሥአተ ቅዱስ

፫ ምሥጢር ዘሥጋሁ ወደሙ ለክርስ

፬ ፫ ቶስ ዘኵሎ ይእኅዝ እግዚአብሔር አምላክነ ።

በዚህም ጽርስፎራ (በሥጋው በደሙ) አድነን ለዓለሙ ሁሉ በምትሆን በአንተ ለዘላለሙ ሕያዋን እንሆን ዘንድ ይ· ሕ· እንደርሱ ።

፺፭ ይ·ካ· የእግዚአብሔር ስሙ ምስጉን ነው በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ ውም ምስጉን ነው የጌትነቱ ስም ይመስገን ይሁን ይሁን የተመሰገነ ይሁን ። ይ· ሕ· እንደርሱ ።

፺፮ ይ· ካ· የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ ላክልን ።

ይ· ሕ· እንደርሱ ።

፺፯ ይ· ዲ· ለጸሎት ተነሡ ።

ይ· ሕ· አቤቱ ይቅር በለን ።

ይ· ካ· ሰላም ለሁላችሁ ይሁን ።

ይ· ሕ· ከመንፈስህ ጋራ ።

፺፰ ይ· ካ· የመፈተት ጸሎት ።

ዳግመኛም ሁሉን የሚይዝ የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን አባት እግዚአብሔርን እንማልዳለን ።

፺፱ ከቅዱስ ምሥጢር በበረከት እንቀበል ዘንድ እንዲሰጠን ለኛ መጽናትን ይስጠን ። ከኛ ወገን ማንንም አያጐስቍል የክርስቶስ ሥጋና ደም የሚሆን ቅዱስ ምሥጢርህን መቀበልን ለሚቀበሉ ሁሉ ተድላ ያድርግላቸው እንጂ ። ይኸውም ሁሉን የሚይዝ አምላካችን እግዚአብሔር ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

፳ ይ· ዲ· ጸልዩ ።

ይ· ሕ· አቡነ ዘበሰማያት ይትቀደስ ስምከ ትምጻእ መንግሥትከ ወይኩን ፈቃድከ በከመ በሰማይ ከማሁ በምድር ሲሳየነ ዘለለዕለትነ ሀበነ ዮም ኅድግ ለነ አበሳነ ወጌጋየነ ከመ ንሕነኒ ንኅድግ ለዘአበሰ ለነ ኢታብአነ እግዚኦ ውስተ መንሱት አላ አድኅነነ ወባልሐነ እምኵሉ እኩይ እስመ ዚአከ ይእቲ መንግሥት ኃይል ወስብሐት ለዓለመ ዓለም ።

፳፩ ይ· ካ· እግዚአብሔር አምላክነ ዘኵሎ ትእኅዝ ንስእለከ ወናስተበቍዐከ ንሥአት ዘቅዱስከ ምሥ

፪ ጢር ጽንዓተ ለነ ተሀበነ ወኢመነኒ እም ውስቴትነ ኢታርስሕ አላ ኵሎ ባርክ በክርስቶስ ።

ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ ስብሐት ወእኂዝ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም አሜን።

፳፪ ይ· ሕ· በከመ ምሕረትከ አምላክነ ወአኮ በከመ አበሳነ በከመ ምሕረትከ አምላክነ ወአኮ በከመ አበሳነ በከመ ምሕረትከ አምላክነ ወአኮ በከመ አበሳነ ።

፳ ይ· ዲ· ጸልዩ ።

ይ· ሕ· አባታችን ሆይ በሰማይ የምትኖር ስምህ ይቀደስ መንግሥትህ ትምጣ ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን የዕለት እንጀራችንን ስጠን ዛሬ በደላችንንም ይቅር በለን እኛ የበደሉንን ይቅር እንድንል ። ወደ ፈተናም አታግባን ከክፉ አድነን እንጂ መንግሥት ያንተ ናትና ኃይልም ምስጋናም ለዘላለሙ ።

፳፩ ይ· ካ· ሁሉን የምትይዝ አምላካችን እግዚአብሔር የቅዱስ ምሥጢርህን መቀበል ለኛ ጽንዕ አድርገህ ትሰጠን ዘንድ እንማልድሃለን ከኛ ወገን ማንንም አታጕስቍል በክርስቶስ ሁሉን ባርክ እንጂ በርሱ ያለ ክብር ጽንዕ ለአንተ ይገባል ከርሱ ጋራ ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ አሜን ።

፳፪ ይ· ሕ· አምላካችን ሆይ እንደ ቸርነትህ ነው እንጂ እንደ ኃጢአታችንም አይደለም አምላካችን ሆይ እንደ ቸርነትህ ነው እንጂ እንደ በደላችን አይደለም አምላካችን ሆይ እንደ ቸርነትህ ነው እንጂ እንደ በደላችን አይደለም ።

www.ethiopianorthodox.org

፷፫ ወእምዝ በተባርዮ ይበሉ ኵሎሙ ፫ተ ጊዜ ።

ሠራዊተ መላእክቲሁ ለመድኃኔ ዓለም ዬ ዬ ዬ ይቀውሙ ቅድሜሁ ለመድኃኔ ዓለም ።

፷፬ ወይኬልልዎ ለመድኃኔ ዓለም ዬ ዬ ዬ ሥጋሁ ወደሙ ለመድኃኔ ዓለም ።

፷፭ ወንብጻሕ ቅድመ ገጹ ለመድኃኔ ዓለም ዬ ዬ ዬ በአሚነ ዚአሁ ለክርስቶስ ንገኒ ።

፪ ወቦ እለ ይብሉ ሐዋርያት ተለዉ አሠሮ ወዝውእቱ ዘያሬድ ።

፷፮ ይ· ዲ· ንፍቅ እንዘ ይበውእ ። አርኅዉ ኆኃተ መኳንንት ።

፷፯ ይ· ዲ· እለ ትቀውሙ አትሕቱ ርእሰክሙ ።

፷፰ ይ· ካ· እግዚአብሔር ዘለዓለም ማእምር ዘኅቡእ ወዘገሃድ ። ቅድሜከ አትሐቱ ርእሶሙ ሕዝብከ ወለከ አግረሩ ቀፈተ ልብ ዘሥጋ ርኢ ዘእምድልው ማኅደርከ ባርክ ኪያሆሙ ወኪያሆን አጽምእ ሎሙ ዕዝነከ ወስምዖሙ ጸሎቶሙ

፷፫ ከዚህ በኋላ ሁሉም እየተቀባበሉ ሦስት ጊዜ ይበሉ ። የመድኃኔ ዓለም አገልጋዮች የሚሆኑ የመላእክት ሠራዊት ዬ ዬ ዬ በመድኃኔ ዓለም ፊት ይቆማሉ ።

፷፬ መድኃኔ ዓለምን ያመሰግኑታል ዬ ዬ ዬ የመድኃኔ ዓለም ሥጋውና ደሙ ።

፷፭ ወደ መድኃኔ ዓለም ፊት እንቅረብ ዬ ዬ ዬ እርሱን በማመን ለክርስቶስ እንገዛለን ። ሐዋርያት ፍለጋውን ተከተሉ የሚሉም አሉ ይኸውም የያሬድ ነው ።

፷፮ ይ· ዲ· ንፍቅ ሲገባ ። መኳንንት ደጆችን ክፈቱ ።

፷፯ ይ· ዲ· የቆማችሁ ሰዎች ራሳችሁን ዝቅ ዝቅ አድርጉ ።

፷፰ ይ· ካ· የተሰወረውንና የተገለጸውን የምታውቅ ዘለዓለማዊ እግዚአብሔር ሆይ ። ወገኖችህ በፊትህ ራሳቸውን ዝቅ ዝቅ አደረጉ ። የሥጋ ልቡናቸውንም አስገዙ ከተዘጋጀ ማደሪያህ ሁነህ እይ። ወንዶችንም ሴቶችንም ባርክ ጆሮህን ቀቅርላቸው ጸሎታቸውንም ስማቸው ።

፳፱ ወአፅንዖ በኃይለ የማንከ ክድን ወርዳእ እምሕመሜ እኩይ ዕቃቤ ሎሙ ኩን ለሥጋነሂ ወለነፍስነሂ ወስክ ሎሙሂ ወለነሂ ሃይማኖተከ ወፈሪሆተ ስምከ ።

፴ በ፩ዱ ወልድከ ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ ስብሐት ወእኂዝ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም አሜን ።

፴፩ ይ· ዲ· ስግዱ ለእግዚአብሔር በፍርሃት ።

ይ· ሕ· ቅድሜከ እግዚኦ ንሰግድ ወንሴብሐከ ።

፴፪ ይ· ካ· ጸሎተ ንስሓ ።

እግዚእ እግዚኦ እግዚአብሔር አብ አኃዜ ኵሉ ዓለም አንተ ውእቱ ዘትፌውስ ቊስለ ነፍስነ ወሥጋነ ወመንፈስነ ።

፴፫ እስመ አንተ ትቤ በአፈ ዋሕድ ወልድከ እግዚእነ ወአምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘይቤሎ ለአቡነ ጴጥሮስ አንተ ኰኵሕ ወዲበ ዛቲ ኰኵሕ አሐንፃ ለቤተ ክርስቲያንየ ቅድስት ወኢይክልዋ አናቅጸ ሲኦል አማስኖታ ወአንቀልቅሎታ ወለከ እሁበከ መራኁተ ዘመንግሥተ ሰማያት ዘአሠርከ በምድር ይኩን እሡረ

፳፱ በቀኝህ ኃይል አጽናቸው ከክፉ ምቀኝነት ሰውራቸው ርዳቸውም ጠባቂ ሁናቸው ለሥጋችንም ለነፍሳችንም ሃይማኖትህንና ስምህን መፍራትን ለሴቶችም ለወንዶችም ጨምርላቸው ።

፴ በአንድ ልጅህ በርሱ ያለ ክብር ጽንዕ ለአንተ ይገባል ከርሱ ጋራ ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ አሜን ።

፴፩ ይ· ዲ· በፍርሃት ሁናችሁ ለእግዚአብሔር ስገዱ ።

ይ· ሕ· አቤቱ በፊትህ እንሰግዳለን እናመሰግንሃለንም ።

፴፪ ይ· ካ· የንስሓ ጸሎት ።

አቤቱ ዓለሙን ሁሉ የያዝህ ጌታችን እግዚአብሔር አብ የነፍሳችንንና የሥጋችንን የደመ ነፍሳችንንም ቊስል የምታድን አንተ ነህ ።

፴፫ ባንድ ልጅህ በጌታችን በአምላካችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አፍ ተናግረሃልና ለአባታችን ለጴጥሮስ እንዲህ ብሎ የተናገረውን አንተ አለት (መሠረት) ነህ በዚህችም አለት (መሠረት) ላይ ክብርት ቤተ ክርስቲያኔን እሠራታለሁ የሲኦልም ደጆች ሊያጠፏትና ሊያነዋውጧት አይችሉም። ላንተም የመንግሥተ ሰማያትን መክፈቻ እሰጥሃለሁ በምድር ያሠርኸው በሰማይ የታሠረ ይሆን ዘንድ

www.ethiopianorthodox.org

በሰማያት ወዘፈታሕከ በምድር
ይኩን ፍቱሐ በሰማያት ።

፻፬ ወይኩኑ ፍቱሓነ ወግዑዛነ ኵሎሙ
አግብርቲከ ወአእማቲከ በበአስማ
ቲሆሙ በአፉሁ ለመንፈስ ቅዱስ
ወበአፈ ዚአየ አነ ገብርከ ኃጥእ
ወአበሲ እመሂ በአእምሮ አው
በኢያእምሮ ገብሩ ።

፻፭ ዕቀቦሙ እግዚኦ ወተማኅፀኖሙ
ለእሉ አግብርቲከ አበውየ ወአኀ
ውየ ወአኃትየ ።

፻፮ ወዓዲ ለትሕትና ዚአየ አነ ገብ
ርከ ኃጥእ ወአባሲ ፍትሐኒ ።

፻፯ ወይኩኑ ፍቱሓነ ወግዑዛነ እም
አፈ ሥሉስ ቅዱስ አብ ወወልድ
ወመንፈስ ቅዱስ ወእምአፈ ዚአየ
አነ ገብርከ ኃጥእ ወአባሲ ።

፻፰ አ መሐሪ ወመስተሣህል ወመፍ
ቀሬ ሰብእ እግዚአብሔር አምላክነ
ዘታአትት ኃጢአተ ዓለም ተወከፍ
ንስሐሆሙ ለአግብርቲከ ወአእማ
ቲከ ወአሥርቅ ላዕሌሆሙ ብርሃነ
ሕይወት ዘለዓለም ወሥረይ ሎሙ
እግዚኦ ኵሎ ኃጢአቶሙ እስመ
ኄር አንተ ወመፍቀሬ ሰብእ ።

፻፱ አ እግዚአብሔር አምላክነ መስተሣ
ህል ርኁቀ መዓት ወብዙኃ ምሕ
ረት ወጻድቅ ሥረይ ሊተ ኃጢአትየ
ለገብርከ ።

በምድርም የፈታኸው በሰ
ማይ የተፈታ ይሆን ዘንድ ።

፻፬ ወንዶቹም ሴቶቹም ባሮችህ ሁሉ
በየስማቸው የተፈቱ ነጻም የወጡ
ይሁኑ በመንፈስ ቅዱስ ቃል ኃጥእ
በደለኛ በምሆን በኔም በባሪያህ
እገሌ ቃል በማወቅ ወይም
ባለማወቅ ቢሠሩ ።

፻፭ አቤቱ እሊህን ባሮችህን አባቶቼንና
ወንድሞቼን እኅቶቼንም አጽንተህ
ጠብቃቸው ።

፻፮ ዳግመኛም ኃጥእ በደለኛ የምሆን
እኔንም ወራዳነቴን አይተህ ፍታኝ።

፻፯ ልዩ ሦስት በሚሆኑ በአብና በወል
ድ በመንፈስ ቅዱስም ቃል የተፈቱ
ነጻም የወጡ ይሁኑ ። ኃጥእ በደ
ለኛ በምሆን በኔም በባሪያህ ቃል ።

፻፰ መሐሪ ይቅር ባይ ሰውንም የምት
ወድ አምላካችን እግዚአብሔር
ሆይ የዓለሙን ኃጢአት የምታርቅ
የወንዶቹንና የሴቶቹን ባሮችህን
ንስሓቸውን ተቀበል። የዘላለም ደኅ
ንነት የሚሆን ብርሃንንም ግለጽላ
ቸው አቤቱ ኃጢአታቸውንም ሁሉ
ይቅር በላቸው ቸር ሰውንም
የምትወድ አንተ ነህና ።

፻፱ ይቅር ባይ አምላካችን እግዚአብ
ሔር ሆይ መዓትህ የራቀ ምሕረት
ህም የበዛ እውነተኛም የምትሆን
የኔን ኃጢአቴን አስተሥርይልኝ ።

www.ethiopianorthodox.org

፹ ወለኵሎሙ አግብርቲከ ወአእማ
ቲከ አድኅኖሙ እምኵሉ አበሳ
ወመርገም ።
ለእመ አበስነ ለከ እግዚኦ እመሂ
በቃልነ ወእመሂ በምግባርነ ወእ
መሂ በሕሊናነ ኅድግ ወሥረይ ወአ
ናኅሲ ወተሣሀል እስመ ኄር አንተ
ወመፍቀሬ ሰብእ እግዚአብሔር
አምላክነ ።

፹፩ ኦ እግዚኦ ረስየነ ፍቱሐነ ወግዑዛነ
ወለኵሎሙ ሕዝብከ ፍትሖሙ
ወሊተኒ ለኃጥእ ገብርከ ፍትሐኒ ።

፹፪ ወእምዝ ይሚጥ ገጾ መንገለ ሕዝብ
ወይዕትቦሙ ሠልሰ ቡራኬ ላዕለ
ሕዝብ ወለእለኒ ሀለዉ ምስሌሁ
ይዝክሮሙ ። ወዓዲ የበል ተዘከሮ
እግዚኦ ለአብ ክቡር ርእሰ ሊቀ
ጳጳሳቲነ አባ እገሌ ። ወብፁዕ ሊቀ
ጳጳስነ አባ እገሌ ። አምላክነ ዐቂበ
ዕቀቦሙ ለነ ዓመታተ ብዙኀ ወመ
ዋዕለ ነዊኀ በጽድቅ ወበሰላም ።

፹፫ ተዘከራ እግዚኦ ለሀገሪትነ ኢትዮ
ጵያ ወዕቀባ በጽድቅ ወበሰላም አግርር
ፀራ ወጸላዕታ ፍጡነ ።

፹፬ ተዘከር እግዚኦ ሊቃነ ጳጳሳት
ጳጳሳተ ኤጲስ ቆጶሳተ ቀሳውስተ
ወዲያቆናተ አናጕንስጢሳውያነ

፹ ወንዶችንና ሴቶችንም ባሮችህንም
ሁሉ ከበደልም ከመርገምም ሁሉ
አድናቸው ። በቃላችንም ቢሆን
በሥራችንም ቢሆን በአሳባችንም
ቢሆን አቤቱ አንተን ብንበድል
ተውልን አስተሥርይልን አቃልል
ልን ይቅርም በለን ።

፹፩ አምላካችን እግዚአብሔር ሆይ
አንተ ቸር ሰውን ወዳጅ ነህና ።
አቤቱ የተፈታን ነጻም የወጣን
አድርገን ወገኖችህንም ሁሉ ፍታ
ቸው ኃጥእ የምሆን እኔንም ባርያ
ህን ፍታኝ ።

፹፪ ከዚህ በኋላ ፊቱን ወደ ሕዝቡ
መልሶ ሕዝቡን ሦስት ጊዜ ይባርካ
ቸው ። ከእነርሱም ጋራ ያሉትን
ስማቸውን ይጥራ ዳግመኛም ይበል ።
ክቡር የሚሆን የጳጳሳቱን አለቃ አባ
እገሌን አስበው ።
ብፁዕ የሚሆን አባ እገሌንም አስ
በው ። አምላካችን ሆይ ለብዙ
ዘመናት ለረጅም ወራት በእውነ
ትና በሰላም መጠበቅ ጠብቅልን ።

፹፫ አቤቱ ሀገራችንንም ኢትዮጵያን
አስባት የሚጣሏትንና ጠላቶቿን
ፈጥነህ አስገዛላት ።

፹፬ የጳጳሳቱን አለቆች ጳጳሳቱንና ኤጲስ
ቆጶሳቱን ቀሳውስቱንና ዲያቆናቱን
አንባቢዎችንና መዘምራኑን ደናግ

www.ethiopianorthodox.org

ወመዘምራነ ደናግለ ወመነኮሳተ ዕቤራተ ወእጓለ ማውታ እደ ወአን ስተ አእሩገ ወሕፃናተ ወኵሎሙ ሕዝበ ክርስቲያን እለ ሀለዉ ወቆሙ ውስተ ዛቲ ቤተ ክርስቲ ያን ቅድስት አፅንዖሙ በሃይማኖተ ክርስቶስ ።

፻፭ በዝየ ይዝክር ሐዲሳነ ሙታነ ። ተዘከሮሙ እግዚኦ ለኵሎሙ አበ ዊነ ወአኃዊነ ወአኃቲነ እለ ኖሙ ወአዕረፉ በርትዕት ሃይማኖት ወደ ምር ነፍሳቲሆሙ ውስተ ኅፅነ አብ ርሃም ይስሐቅ ወያዕቆብ ።

፻፮ ወለነኒ አድኅነነ እምኵሉ አበሳ ወመርገም ወእምኵሉ ጌጋይ ወእ ምኵሉ ክሕደት ወእምክሉ መሐላ በሐሰት ወእምኵሉ ግዘት ወእም ተደምሮ በዕልወት ወርኵስ ምስለ ዓላውያን ወአረማውያን ።

፻፯ ጸግወነ እግዚኦ ጥበበ ወኃይለ ልበ ወልቡና ወአእምሮ ከመ ንርኃቅ ወንጕየይ እንከ እስከ ለዝሉፉ እምኵሉ ምግባራቲሁ ለሰይጣን ዘየሚክር ።

፻፰ ሀበነ እግዚኦ ንግበር ፈቃደከ ወሥምረተከ በኵሉ ጊዜ ወጸሐፍ አስማቲነ ውስተ መጽሐፈ ሕይ ወት በመንግሥተ ሰማያት ምስለ ኵሎሙ ቅዱሳን ወሰማዕት በኢየ

ሉንና መነኰሳቱን ባልቴቶቹንና አባት እናት የሞቱባቸውን ወንዶ ቹንና ሴቶቹን ሽማግሌዎቹንና ልጆ ቹን ክብርት በምትሆን በዚህች ቤተ ክርስቲያን ያሉትን የቆሙት ንም የክርስቲያንን ወገኖች ሁሉ ክርስቶስን በማመን አጽናቸው ።

፻፭ ከዚህ ሲደርስ አዲስ የሞቱትን ያንሣ ። አቤቱ በቀናች ሃይማኖት ሁነው የሞቱትንና ያረፉትን አባቶ ቻችንንና ወንድሞቻችንን እኅቶቻ ችንንም ሁሉ አስባቸው ። ነፍሶቻ ቸውንም በአብርሃምና በይስሐቅ በያዕቆብም አጠገብ አኑር ።

፻፮ እኛንም ከኃጢአት ሁሉ ከመርገ ምም ከበደልም ሁሉ ከክሕደትም ሁሉ በሐሰትም ከመማል ሁሉ ከመገዘትም ሁሉ አድነን ። በክሕደትና በርኵሰት ከዓላውያንና ከአረማውያን ጋራ አንድ ከመሆን አድነን ።

፻፯ አቤቱ ጥበብንና ኃይልን ልብንና ልቡናን ዕውቀትንም ስጠን ። እንግዲህ ከሚፈታተነን ከሰይጣን ሥራ ሁሉ እስከ ዘላለሙ እንርቅ እንሸሽም ዘንድ ።

፻፰ አቤቱ ሁልጊዜ ፈቃድህን ውድህ ንም እንሠራ ዘንድ ስጠን ። ስማችንንም በመንግሥተ ሰማያት በሕይወት መጽሐፍ ከቅዱሳንና ከሰማዕታት ሁሉ ጋራ ጻፍ በጌታ

www.ethiopianorthodox.org

ሱስ ክርስቶስ እግዚእነ ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ ስብሐት ወእኂዝ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም አሜን ።

፹፱ ፩ ይ· ዲ· ነጽር ።

፺ ፩ ፩ ይ· ካ· ቅድሳት ለቅዱሳን ።

ይ· ሕ· ፩ዱ አብ ቅዱስ ፩ዱ ወልድ ቅዱስ ፩ዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ።

፺፩ ይ· ካ· እግዚአብሔር ምስለ ኵልክሙ ።

ይ· ሕ· ምስለ መንፈስከ ።

፺፪ ወእምዝ ያንሥእ ካህን ኅስብተ ፍጹመ በእዴሁ ወይበል ፫ተ ጊዜ በልዑል ዜማ ።

፺፫ እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ ።
እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ ።
እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ ።

ይ· ሕ· ከማሁ ።

ይ· ካ· እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ
እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ ።
እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ
እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ
እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ ።

፲ተ ወ፭ተ ጊዜ በንኡስ ዜማ ።

ይ· ሕ· ከማሁ ።

ወእምዝ ይ· ካ· እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ ።

ችን በኢየሱስ ክርስቶስ በርሱ ያለ ክብር ጽንዕ ለአንተ ይገባል ከርሱ ጋራ ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ አሜን ።

፹፱ ይ· ዲ· ተመልከት ።

፺ ይ· ካ· ቅድሳት ለቅዱሳን ።

ይ· ሕ· ቅዱስ አብ አንድ ነው ቅዱስ ወልድም አንድ ነው መንፈስ ቅዱስም አንድ ነው ።

፺፩ ይ· ካ· እግዚአብሔር ከሁላችሁ ጋራ ይሁን ።

ይ· ሕ· ከመንፈስህ ጋራ ።

፺፪ ከዚህም በኋላ ቄሱ መላውን ኅብስት አንሥቶ በእጁ ይዞ እንዲህ ይበል ። ሦስት ጊዜ በዜማ አሰምቶ

፺፫ አቤቱ ክርስቶስ ማረን ።
አቤቱ ክርስቶስ ማረን ።
አቤቱ ክርስቶስ ማረን ።

ይ· ሕ· ከማሁ ።

ይ· ካ· አቤቱ ክርስቶስ ማረን ።
አቤቱ ክርስቶስ ማረን ።
አቤቱ ክርስቶስ ማረን ።
አቤቱ ክርስቶስ ማረን ።
አቤቱ ክርስቶስ ማረን ።

ዐሥራ አምስት ጊዜ በንኡስ ዜማ ።

ይ· ሕ· ከማሁ ።

ይ· ካ· አቤቱ ክርስቶስ ማረን ።

www.ethiopianorthodox.org

እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ ።

ይ· ሕ· ከማሁ ።

ይ· ካ· እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ ።

፺፬ ይ· ዲ· ጸሎተ እለ ውስተ ንስሐ ሀለውክሙ አትሕቱ ርእሰክሙ ።

፺፭ ወእምዝ ተመይጦ መንገለ ሕዝብ ።

ይ· ካ· እግዚአብሔር አምላክነ ነጽር ዲበ ሕዝብከ እለ ውስተ ንስሓ ሀለዉ ወተሣሃሎሙ በከመ ዕበየ ሣህልከ ወበከመ ብዙኀ ምሕረትከ ደምስስ አበሳሆሙ ክድኖሙ ወዕቀቦሙ እምኵሉ እኩይ ።

፺፮ ወቤዙ ነፍሳቲሆሙ በሰላም አኀዊረከ ዘቀዳሚ ምግባሮሙ ደምሮሙ ውስተ ቤተ ክርስቲያንከ ቅድስት በሞገሱ ወበምሕረቱ ለዋሕድ ወልድከ እግዚእነ ወአምላክነ ወመድኀኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ ስብሐት ወእኂዝ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም አሜን ።

(በንባብ)

፺፯ ይ· ዲ· ተንሥኡ ለጸሎት ።

ይ· ሕ· እግዚኦ ተሣሃለነ ።

ይ· ካ· ሰላም ለኵልክሙ ።

ይ· ሕ· ምስለ መንፈስከ ።

፺፰ ይ· ካ· ሥጋ ቅዱስ ዘበአማን ዝ "እማሬ" ውእቱ ዘእግዚእነ ወአምላክነ ወመድኀኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘይትወሀብ ለሕይወት ወለመድኀ

አቤቱ ክርስቶስ ማረን ።

ይ· ሕ· ከማሁ ።

ይ· ካ· አቤቱ ክርስቶስ ማረን ።

፺፬ ይ· ዲ· በንስሓ ውስጥ ያላችሁ ራሳችሁን ዝቅ ዝቅ አድርጉ ።

፺፭ ከዚህ በኋላ ወደ ሕዝቡ ተመልሶ ።

ይ· ካ· አምላካችን እግዚአብሔር ሆይ በንስሓ ውስጥ ወዳሉት ወገኖች ተመልከት ። እንደ ይቅርታህም ብዛት ይቅር በላቸው ። እንደ ቸርነትህም ብዛት በደላቸውን አጥፋላቸው ከክፉ ነገርም ሁሉ ጠብቃቸው ሰውራቸውም ።

፺፮ የቀደመ ሥራቸውን ይቅር ብለህ በሰላም ነፍሳቸውን አድን ከቅድስት ቤተ ክርስቲያንህ አንድ አድርጋቸው ተቀዳሚ ተከታይ በሌለው ባንድ ልጅህ በጌታችንና በአምላካችን በመድኃኒታችንም በኢየሱስ ክርስቶስ በይቅርታውና በምሕረቱ ከቅድስት ቤተ ክርስቲያንህ ጨምራቸው ። በርሱ ያለ ክብር ጽንዕ ለአንተ ይገባል ከርሱ ጋራ ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ አሜን ።

፺፯ ይ· ዲ· ለጸሎት ተነሡ ።

ይ· ሕ· አቤቱ ይቅር በለን ።

ይ· ካ· ሰላም ለሁላችሁ ይሁን ።

ይ· ሕ· ከመንፈስህ ጋራ ።

፺፰ ይ· ካ· በእውነት ክቡር የሚሆን የጌታችንና የአምላካችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ ይህ "እማሬ" ነው። አምነው ከርሱ ለሚ

www.ethiopianorthodox.org

ኒት ወለሥርየተ ኃጢአት ለእለ ይነ
ሥኡ እምኔሁ በአሚን ።
ይ· ሕ· አሜን ።
፺፱ ይ· ካ· ደም ክቡር ዘበአማን ዘ
"እማሬ" ውእቱ ዘእግዚእነ ወአም
ላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስ
ቶስ ዘይትወሀብ ለሕይወት ወለመ
ድኃኒት ወለሥርየተ ኃጢአት ለእለ
ይትሜጠዉ እምኔሁ በአሚን ።
ይ· ሕ· አሜን ።
፻ ይ· ካ· እስመ ዝንቱ "እማሬ"
ውእቱ ሥጋሁ ወደሙ ለአማኑኤል
አምላክነ ዘበአማን ።
ይ· ሕ· አሜን ።
፻፩ ይ· ካ· አአምን አአምን አአምን
ወእትአመን እስከ ደኃሪት እስትን
ፋስ ከመ ዝንቱ "እማሬ" ውእቱ
ሥጋሁ ወደሙ ለእግዚእነ ወአምላ
ክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ
ዘነሥአ እምእግዝእት ኵልነ ቅድ
ስት ድንግል በ፪ኤ ማርያም ወረ
ሰዮ ፩ደ ምስለ መለኮቱ ዘእንበለ
ቱስሕት ወኢትድምርት ዘእንበለ
ፍልጠት ወኢውላጤ ወኮነ ሰማ
ዕተ በስምዕ ሠናይ በመዋዕለ ጲላ
ጦስ ጴንጤናዊ ወመጠዎ በእንቲ
አነ ወበእንተ ሕይወተ ኵልነ ።
ይ· ሕ· አሜን ።
፻፪ ይ· ካ· አአምን አአምን አአምን

ቀበሉ ሕይወትና መድኃኒት የኃጢ
አት ማስተሥረያም ሊሆን የሚሰጥ።
ይ· ሕ· አሜን ።
፺፱ ይ· ካ· በእውነት አምነው ከርሱ
ለሚቀበሉ ሕይወትና መድኃኒት
የኃጢአት ማስተሥረያም ሊሆን
የሚሰጥ የጌታችንና የአምላካችን
የኢየሱስ ክርስቶስ ክቡር ደም ይህ
"እማሬ" ነው ።
ይ· ሕ· አሜን ።
፻ ይ· ካ· በእውነት የአምላካችን
የአማኑኤል ሥጋውና ደሙ ይህ
"እማሬ" ነውና ።
ይ· ሕ· አሜን ።
፻፩ ይ· ካ· አምናለሁ አምናለሁ
አምናለሁ ። እስከ መጨረሻዪቱም
እስትንፋስ እታመናለሁ በሁለት
ወገን ድንግል ከምትሆን ከሁላችን
እመቤት ከቅድስት ማርያም የነ
ሣው የጌታችንና የአምላካችን የመ
ድኃኒታችንም የኢየሱስ ክርስቶስ
ሥጋው ደሙ ይህ "እማሬ" እንደ
ሆነ ያለመቀላቀልና ያለትድምርት
ያለመለወጥና ያለመለየት ከመለ
ኮቱ ጋራ አንድ ያደረገው በጴንጤ
ናዊ ጲላጦስም ዘመን ባማረ ምስክ
ርነት ምስክር የሆነ ስለ እኛና ስለ
ሁላችንም ሕይወት አሳልፎ የሰ
ጠው ።
ይ· ሕ· አሜን ።
፻፪ ይ· ካ· አምናለሁ አምናለሁ አምና

www.ethiopianorthodox.org

ወእትአመን ከመ ኢተፈልጠ መለ
ኮቱ እምትስብእቱ ኢአሐተ ሰዓተ
ወኢ ከመ ቅጽበተ ዓይን አላ
መጠዎ በእንቲአነ ለሕይወት ወለ
መድኃኒት ወለሥርየተ ኃጢአት
ለእለ ይትሜጠዉ እምኔሁ በአሚን
ይ· ሕ· አሜን ።

፻፫ ይ· ካ· አአምን አአምን አአምን
ወእትአመን ከመ ዝንቱ "እማሬ"
ውእቱ ሥጋሁ ወደሙ ለእግዚእነ
ወአምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ
ክርስቶስ ዝ ውእቱ ዘሎቱ ይደሉ
ክብር ወስብሐት ወስግደት ምስለ
አቡሁ ኄር ሰማያዊ ወመንፈስ
ቅዱስ ማሕየዊ ይእዜኒ ወዘልፈኒ
ወለዓለመ ዓለም አሜን ።

፻፬ ወእምዝ ይነሣእ ካህን በእዴሁ
ዓስበ ዲያቆን ዘቦቱ ትእምርተ
መስቀል ወይደዮ ውስተ ጽዋዕ
ወይጥማዕ ቦቱ ደመ ወይዕትብ
ሥጋ በትእምርተ መስቀል ቅድመ
ዲበ ክፍል ዐቢይ እንተ አፍአሁ
ወዳግመ እንተ ውስጡ ወሣልሰ
ዲበ ክፍል ንኡስ ወካዕበ ይዕትብ
በሥጋ ደመ እንዘ ይብል ቡሩክ
እግዚአብሔር እስከ ተፍጻሜቱ ።
ወያምጽእ ንፍቅ ዲያቆን ማየ ለካህ
ናት ወይትሐፀቡ እደዊሆሙ አም
ሳለ ቅዱሳን በነፍሶሙ ።

ለሁ ። መለኮቱ ከሰውነቱ አንዲት
ሰዓት እንኳን እንደ ዓይን ቅጽበ
ትስ ስንኳ እንዳልተለየም እታመና
ለሁ ስለኛ ሰጠው እንጂ ለሕይወ
ትና ለመድኃኒት ለኃጢአትም ማስተ
ሥረያ ሊሆን አምነው ለሚቀበሉ
ሰዎች ስለኛ አሳልፎ ሰጠው እንጂ
ይ· ሕ· አሜን ።

፻፫ ይ· ካ· አምናለሁ አምናለሁ አምና
ለሁ የጌታችንና የአምላካችን የመ
ድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ
ሥጋው ደሙ ይህ "እማሬ" እንደ
ሆነ እታመናለሁ ። ክብርና ምስጋና
ስግደትም ቸር ከሚሆን ከሰማያዊ
አባቱ ጋራ ማሕየዊ ከሚሆን ከመ
ንፈስ ቅዱስ ጋራ የሚገባው ይህ
ነው ። ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ
አሜን ።

፻፬ ከዚህ በኋላ ካህኑ ትእምርተ
መስቀል ያለበትን ዓስበ ዲያቆን
በእጁ አንሥቶ ከጽዋው ይጨም
ረው በርሱ ደሙን ጠምቶ ሥጋ
ውን በትእምርተ መስቀል ይባርክ ።
አስቀድሞ በአፍኣው ያለውን ታላ
ቁን ክፍል ሁለተኛም የውስጡን
ክፍል ሦስተኛም ታናሹን ክፍል ።
ዳግመኛም እስከ መጨረሻው ቡሩክ
እግዚአብሔር እያለ በሥጋው
ደሙን ይባርክ ። ንፍቅ ዲያቆን
ለካህናቱ ውኃ ያቅርብ ። በነፍሳቸው
ቅዱሳን ለመሆናቸውም አምሳል
እጃቸውን ይታጠቡ ።

www.ethiopianorthodox.org

፻፳ ወእምዝ ይበል ዘንተ ጸሎተ ።
እግዚአብሔር አምላኪየ ናሁ ሥጋ ወልድከ መሥዋዕት ዘያሠምረከ ወበዝንቱ አናኅሲ ሊተ ኵሎ ኃጢአትየ እስመ በእንቲአየ ሞተ ወልድከ ዋሕድ ።

፻፳ ከዚህም በኋላ ይህን ጸሎት ይበል ። አምላኬ እግዚአብሔር ሆይ ደስ የሚያሰኝህ መሥዋዕት የልጅህ ሥጋ እነሆ ። በዚህም ኃጢአቴን ሁሉ አቃልልኝ ስለ እኔ አንድ ልጅህ ሙቷልና ።

፻፳፩ ወናሁ ደመ መሢሕከ ንጹሕ ዘተክዕወ በእንቲአየ በቀራንዮ ይኬልሕ ህየንቴየ ዝንቱ ደም ነባቢ ይኩን ሠራዪ ኃጢአትየ ለገብርከ ።

፻፳፩ ስለ እኔ በቀራንዮ የፈሰሰ ንጹሕ የሚሆን የመሢህም ደም እነሆ ስለ እኔ ይጮኻል ። ይህ የሚናገር ደም የኔን የባሪያህን ኃጢአት የሚያስተ ሠርይ ይሁን ።

፻፳፪ ወተወከፍ ስእለትየ በእንቲአሁ እስመ በእንቲአየ ኵናተ ወቅንዋተ ተወከፈ ፍቁርከ ወሐመ ከመ ያሥ ምርከ ወእምድኅረ ድኅንኩ ገብአ ሰይጣን ውስተ ልብየ ወነደፈኒ በአሕፃሁ ሀበኒ እግዚኦ ምሕረተከ እስመ መስተዋቅስ ጽኑዕ ውእቱ ።

፻፳፪ ስለ እነርሱም ልመናዬን ተቀበል ። ወዳጅህ ስለ እኔ ጦርንና ቅንዋትን ተቀብሏልና ደስ ያሰኝህም ዘንድ ታመመ ። ከዳንሁም በኋላ ሰይጣን ወደ ልቡናዬ ተመልሶ በፍላፆቹ ወጋኝ አቤቱ ምሕረትህን ስጠኝ ጽኑ ከሳሽ ነውና ።

፻፳፫ ወበስንቀ ኃጢአት ቀተለኒ ተበቀል ሊተ እምደፋሪ ዘኢይጸግብ አስሕ ቶትየ እምሕይወትየ ።

፻፳፫ ኃጢአትንም ምክንያት (ሥንቅ) አድርጎ ገደለኝ እኔን ከሕይወቴ ማሳ ትን በቃኝ ከማይል ደፋር አድነኝ ።

፻፳፬ አንተ እግዚኦ ንጉሥየ ወአምላኪየ ወመድኃንየ አጽምም ሊተ ቍስለ ነፍስየ ወሥጋየ ለገብርከ ።

፻፳፬ አቤቱ ንጉሤና አምላኬ መድኃኒቴም የምትሆን አንተ የእኔን የባርያህን የነፍሴንና የሥጋዬን ቍስል አድር ቅልኝ ።

፻፳፭ ወእምቅድመ ተመጥዎ ቍርባን ይበሉ ኵሎሙ እለ ይነሥኡ እም ሥጢር ቅዱስ ።

፻፳፭ ቍርባኑን ከመቀበል አስቀድሞ ከቅዱስ ምሥጢር የሚቀበሉ ሁሉ እንዲህ ይበሉ ።

አ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ አኮ ዘይደልወኒ ትባእ ታሕተ ጠፈረ

አቤቱ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ርኵሰት ከሆነች ከቤቴ ጠፈር

www.ethiopianorthodox.org

ቤትየ ርኵስት እስመ አነ አስተቈ
ጣዕኩከ ወገበርኩ እኩየ በቅድ
ሜከ ወአርኰስኩ ነፍስየ ወሥጋየ
ዘፈጠርከ በአርአያከ ወበአምሳሊከ
በዐሊወ ትእዛዝከ ወአልብየ ምግ
ባረ ሠናይ ወኢምንትኒ ።

፻፲፩ ወባሕቱ በእንተ ተኬንዎትከ ወበ
እንተ ትስብእትከ በእንተ መድኃኒ
ትየ ወበእንተ መስቀልከ ክቡር ወበ
እንተ ሞትከ ማሕየዊት ወበእንተ
ትንሣኤከ በሣልስት ዕለት እስእለከ
ወአስተበቍዐከ ኦ እግዚእየ ከመ
ታንጽሐኒ እምኵሉ አበሳ ወመርገም
ወእምኵሉ ኃጢአት ወርኵስ ።

፻፲፪ ወሶበ እትሜጦዎ ለምሥጢረ
ቅድሳቲከ ኢይኩንኒ ለቅስት ወኢ
ለኵነኔ አላ መሐረኒ ወተሣሃለኒ
ወሀበኒ ቦቱ ሥርየተ ኃጢአትየ
ወሕይወተ ነፍስየ ኦ ሕይወተ ዓለም
በስእለታ ለእግዝእትነ ቅድስት
ድንግል በ፪ኤ ማርያም ወላዲትከ
ወዮሐንስ መጥምቅ ወበጸሎተ
ኵሎሙ ቅዱሳን መላእክት ወኵ
ሎሙ ሰማዕት ወጻድቃን መስተጋ
ድላን ለሠናይ እስከ ለዓለመ ዓለም
አሜን ።

፻፲፫ ይ· ካ· እንዘ ይትሜጦ ለባሕቲቱ ።
ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ
ኢይኩን ዝንቱ ምሥጢርከ አበሳ

በታች ትገባ ዘንድ የሚገባኝ አይደ
ለም። እኔ አሳዝኜሃለሁና በፊትህም
ክፉ ሥራ ሠርቻለሁና በአርአያህና
በአምሳልህ የፈጠርኸው ሥጋዬንና
ነፍሴን ትእዛዝህን በማፍረስ
አሳድፌአለሁና ሥራም ምንም ምን
የለኝምና ።

፻፲፩ ነገር ግን ስለ መፍጠርህና እኔን
ለማዳን ሰው ስለ መሆንህ ስለ ክቡር
መስቀልህም ማሕየዊት ስለ ምትሆን
ስለ ሞትህ በሦስተኛው ቀን ስለ
መነሣትህም ጌታዬ ሆይ ከበደልና
ከመርገም ሁሉ ከኃጢአትና ከርኵሰ
ትም ሁሉ ታነጻኝ ዘንድ እለምንሃ
ለሁ እማልድሃለሁም ።

፻፲፪ የቅድስናህንም ምሥጢር በተቀበል
ሁት ጊዜ ለወቀሳ ለመፈራረጃ
አይሁንብኝ ማረኝ ይቅርም በለኝ
እንጂ። የዓለም ሕይወት ሆይ በርሱ
የኃጢአቴን ሥርየት የነፍሴንም
ሕይወት ስጠኝ እንጂ ። በሁለት
ወገን ድንግል በምትሆን በወለደ
ችህ በእመቤታችን በቅድስት ማር
ያም በመጥምቁ በዮሐንስም አማላ
ጅነት ክቡራን በሚሆኑ በመላእክ
ትም በሰማዕታትና ለበጎ ነገር በሚ
ጋደሉ በጻድቃንም ሁሉ ጸሎት
እስከ ዘላለሙ ድረስ አሜን ።

፻፲፫ ይ· ካ· ሲቀበልም ለብቻው ።
ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ይህ
ምሥጢርህ በእኔ በደል አይሁንብኝ

www.ethiopianorthodox.org

ላዕሌየ አላ ይኩን ለአንጽሖ ነፍስየ ወሥጋየ ።

፻፲፬ ወእምዝ ይትመጠ ቅድመ ቊርባነ ለሊሁ ወካዕበ ይመጡ ለንፍቅ ካህን ወንፍቅሂ የሀቦ ደመ ለካህን ወእምዝ ይንሣእ ለሊሁ በእዴሁ ደመ ንፍቅ ካህን ወእምዝ ይመጡ ለካህናት ውእቱ ካህን ሥጋ ወንፍቅሂ ደመ ።

፻፲፭ ይ· ካ· እንዘ ይሜጡ በቅዳሴ እግዚእ ። ሥጋሁ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ለቀድሶ ሥጋ ወነፍስ ወመንፈስ ።

ወበቅዳሴ ሐዋርያት ።

ኅብስተ ሕይወት ዘወረደ እምሰማያት ቅዱስ ሥጋሁ ለክርስቶስ ።

ወበቅዳሴ ሊቃውንት ።

ሥጋሁ ለአማኑኤል አምላክነ ዘበአማን ዘነሥአ እምእግዝእተ ኵልነ ማርያም ።

ዘይቀርብሂ ይበል "አሜን" ።

፻፲፮ ቅድመ ይቅረቡ ሊቃነ ጳጳሳት ጳጳሳት ወኤጲስ ቆጶሳት ወእምድኅሬሆሙ ቀሳውስት ወዲያቆናት ወካዕበ ኵሎሙ በበመዓርጊሆሙ ወእምድኅረ እደው ይትመጠዋ አንስት ሕፃናትሰ እለ ይጠመቁ ይትመጠዉ እምቅድመ ሕዝብ ።

ሥጋዬንና ነፍሴን ለማንጻት ይሁን ልኝ እንጂ ።

፻፲፬ ከዚህም በኋላ አስቀድሞ ቊርባኑን ራሱ ይቀበል ዳግመኛም ለንፍቁ ካህን ያቀብል ንፍቁም ደሙን ለካህኑ ያቀብለው ። ከዚህም በኋላ ንፍቁ ካህን ደሙን እርሱ በእጁ ይቀበል ከዚህ በኋላ ያው (ሠራዒው) ካህን ሥጋውን ለካህናቱ ያቀብል ንፍቁም ደሙን ።

፻፲፭ ይ· ካ· ሲያቀብል በጌታችን ቅዳሴ ሥጋንና ነፍስን ደመ ነፍስንም ለማክበር የሚሆን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ ይህ ነው ።

በሐዋርያትም ቅዳሴ ።

ከሰማይ የወረደ የሕይወት ኅብስት የሚሆን የክርስቶስ ክቡር ሥጋ ።

በሊቃውንት ቅዳሴ ።

ከሁላችን እመቤት ከማርያም የነሣው እውነተኛ የሚሆን የአምላካችን የአማኑኤል ሥጋ ።

የሚቀበለውም አሜን ይበል ።

፻፲፮ አስቀድሞ ሊቃነ ጳጳሳትና ጳጳሳት ኤጲስቆጶሳት ከነርሱም በኋላ ቀሳውስትና ዲያቆናት ይቊረቡ ። ዳግመኛም ሁሉ በየማዕርጋቸው ይቊረቡ ። ከወንዶችም በኋላ ሴቶች ይቀበሉ የሚጠመቁ ሕፃናት ግን ከሕዝቡ አስቀድሞ ይቀበሉ ።

www.ethiopianorthodox.org

፻፲፯ ወእምድኅረ ተመጥዎ ቍርባን እንዘ ሀሎ በአፉሁ ይበል ኵሉ ለለ፩ዱ ፩ዱ ።

ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ሥሉስ ዘኢይትነገር ሀበኒ ከመ እንሣእ ለሕይወት ዘንተ ሥጋ ወደመ ዘእንበለ
፩ ኵነኔ ሀበኒ እግበር ፍሬ ዘየሠምረከ ከመ አስተርኢ በስብሐቲከ
፩ ወእሕየው ለከ እንዘ እገብር ዘዚአከ ፈቃደ ።

፻፲፰ በተአምኖ እጼውዐከ አብ ወእጼውዕ መንግሥተከ ይትቀደስ እግዚኦ ስምከ በላዕሌነ እስመ ኃያል
፩ አንተ እኩት ወስቡሕ ወለከ ስብሐት ለዓለመ ዓለም ። ኢትርግፅ

፻፲፱ ወእምዝ ይብላዕ ዘተመጠወ ወጊዜ ተመጥዎቱ ይደሉ ከመ ያንብር እዴሁ ዲበ አፉሁ ወይሕኪ በሉዋሳስ እስከ ያጸሪ አፉሁ በፍርሃት ወበረዓድ ።

ወእምዝ ይበል ።

ምላእ አፉየ ስብሐተ ወልብየ ኃሤተ ወነፍስየ ትፍሥሕተ ለዘተመጠኩ እምዝንቱ ምሥጢር አምላካዊ ዘኮነ ሰብአ በእንተ መድኃኒተ ሰብእ ።

፻፲፯ ቍርባን ከተቀበለ በኋላ በአፉ ሳለ ሁሉም እያንዳንዱ እንዲህ ይበል ።

የማይነገር ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ሦስት የምትሆን ይህን ሥጋና ደም ሕይወት ሊሆነኝ ሳይፈረድብኝ እቀበል ዘንድ ስጠኝ ። በጌትነትህ እንድገለጽ ደስ የሚያሰኝህን ፍሬ እሠራ ዘንድ ስጠኝ የአንተንም ፈቃድ እየሠራሁ እኖርልህ ዘንድ ስጠኝ ።

፻፲፰ በማመን አባት ብዬ እጠራሃለሁ መንግሥትህንም እጠራለሁ ። አቤቱ ስምህ በኛ ላይ ይመስገን ምስጉን ክቡር የምትሆን ኃያል አንተ ነህና ለአንተ ክብር ይገባሃል ለዘላለሙ ።

፻፲፱ ከዚህ በኋላ የተቀበለውን ይብላ በሚቀበልበትም ጊዜ እጁን ከአፉ ላይ አኑሮ ቀስ ቀስ እያለ ያላም ጠው በመፍራትና በመንቀጥቀጥ ሁኖ አፉን እስኪያጸራ ድረስ ።

ከዚህም በኋላ እንዲህ ይበል ።

ሰውን ለማዳን ሰው ከሆነ ከአምላካዊ ምሥጢር በተቀበልሁ በእኔ በአንደበቴ ምስጋናህን በልቡናዬ ሐሤትን በሰውነቴም ደስታን ምላ ።

www.ethiopianorthodox.org

፻፳ ወይበል ንፍቅ ቀሲስ እንዘ ይሜጡ ደመ ዝንቱ ጽዋዐ ሕይወት ዘወረደ እም ሰማያት ክቡር ደሙ ለክርስ ቶስ ።

ወዘይትሜጦ ይበል አሜን ወአሜን

፻፳፩ ጸሎት ዘባስልዮስ ወትእዛዝ ዘሀገርነ ወእንዘ ሀሎ ደም በአፉሁ ይበል በሕሊናሁ ።

አ እግዚእየ ወአምላኪየ ኢየሱስ ክርስቶስ ናሁ ተመጦኩ ሥጋከ ንጹሐ ወደመከ ክቡረ ይኩነኒ ለሥርየተ ኃጣውእየ ወለኅድገተ አበሳየ ።

፻፳፪ አ ወልድ ዋሕድ ወመፍቀሬ ሰብእ ምላእ አፉየ ስብሐቲከ ከመ እሰብሕ አኰቴተከ እስመ አንተ ቀዳሚ ዘተሰባእከ ወተሰባሕከ ቦቱ ከመ ታድኅነኒ እስከ ለዓለመ ዓለም ወአድኃንከኒ በእንተ ስምከ ቅዱስ ለዓለመ ዓለም ።

፻፳፫ ስብሐት ለከ አ እግዚእየ ወአምላኪየ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘወሀብከኒ ዕሩየ በእደ ዚአሁ ለገብርከ እሴብሐከ ወእስእለከ ከመ እኩን ውስተ መርዔትከ ወከመ ትኆልቁኒ ምስለ አባግዒከ ወተወከፈኒ ።

፻፳፬ ይእዜኒ ኢትዝክር ሊተ አበሳየ አአዙቶ ለጸጋ ዚአከ ዘተውህበ

፻፳ ንፍቅ ቄስም ደሙን ሲያቀብል ይበል ።

ይህ የሕይወት ጽዋ ከሰማይ የወረደ የክርስቶስ ክቡር ደሙ ነው ።

የሚቀበለውም ይበል አሜን ወአ ሜን ።

፻፳፩ የባስልዮስ ጸሎት ያገራችንም ትእዛዝ ነው ። ደሙ በአፉ ሳለ በሕሊናው ይበል ።

ጌታዬ አምላኬም ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ንጹሕ ሥጋህንና ክቡር ደምህን እነሆ ተቀበልሁ ለኃጢአቴ ማሥተሥረያ ይሁነኝ ስለ በደሌም ሁሉ ።

፻፳፪ ሰውን የምትወድ ወልድ ዋሕድ ሆይ ምስጋናህን በአንደበቴ ምላ ምስጋናህን አመሰግን ዘንድ ቀድሞ አንተ ሰው የሆንህ በርሱም የተገለጽህ እስከ ዘላለሙ ታድነኝ ዘንድ ነውና ስለ ቅዱስ ስምህም ለዘላለሙ አዳንኸኝ ።

፻፳፫ ጌታዬ አምላኬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ በአገልጋይህ እጅ ሥጋህንና ደምህን አንድ አድርገህ ለሰጠኸኝ ለአንተ ምስጋና ይገባል ። አመሰግ ንሃለሁ እለምንሃለሁ ከምእመናን ጋራ አንድ እሆን ዘንድ ከበጎችህም ትቆጥረኝ ዘንድ ተቀበለኝ።

፻፳፬ አሁንም ኃጢአቴን አትቍጠር ብኝ ለእኔ የተሰጠኝን ጸጋህንና

www.ethiopianorthodox.org

ሊተ ወለረድኤትከ እንተ ኮነት ምስሌየ ።

፻፳፭ ይበል ዲያቆን እንዘ ይትሜጦ ጽዋዐ ። ጽዋዐ ሕይወት እትሜጦ ወስመ እግዚአብሔር እጼውዕ ።

ወእምዝ ይበል ።

ጸልዩ በእንቲአነ ወበእንተ ኵሎሙ ክርስቲያን እለ ይቤሉነ ግበሩ ተዝካሮሙ በሰላም ወበፍቅረ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰብሑ ወዘምሩ ።

፻፳፮ ወእምዝ ይዘምሩ ካህናት በስብሐተ መዝሙር ዘ፻ወ፶ ወኢያጽርዑ አላ በበ፩ አው በበ፪ ይዘምሩ ።

፻፳፯ ይ· ካ· እንዘ ይወዕእ እለ ጸዋዕከ እግዚአ ወእለ ቀደስከ ክፍል በጽዋዔከ ወአጽንዕ በኃይልከ ወዕቀብ በፍቅርከ ወደምር ውስተ ዘለዓለም መንግሥትከ በክርስቶስ ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ ስብሐት ወእኂዝ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም አሜን።

፻፳፰ ወይዕትብ እንዘ ይወዕእ ዲበ ገሕል ፩ደ ጊዜ ። ወእምዝ ይመጡ ለሕዝብ ውእቱ ካህን ሥጋ ወዲያቆን ደመ ወእንዘ ይሜጡ ይበል ከመ ቀዳሚ ። ወሕዝብኒ እንዘ ይትሜጠዉ ይበሉ አሜን ፩ደ ጊዜ ዲበ ሥጋ ወ፪ተ ጊዜ ዲበ ደም ።

በእኔ ያለች ረድኤትህን አመሰግናለሁ ።

፻፳፭ ዲያቆን ጽዋውን ሲቀበል እንዲህ ይበል ። የሕይወት ጽዋን እቀበላለሁ የእግዚአብሔርንም ስም እጠራለሁ ።

ከዚህ በኋላ እንዲህ ይበል ።

ስለ እኛና መታሰቢያቸውን አድርጉ ስላሉን ስለ ክርስቲያን ሁሉ ጸልዩ በሰላም በኢየሱስ ክርስቶስም ፍቅር አመስግኑ ዘምሩም ።

፻፳፮ ከዚህ በኋላ ካህናት በ፻፶ኛው መዝሙር ምስጋና ይዘምሩ ። አንዳንድ ወይም ሁለት ሁለት እየሆኑ ይዘምሩ እንጂ አያስታጕሉ ።

፻፳፯ ይ· ካ· ሲወጣ አቤቱ የጠራሃቸውን ያከበርሃቸውንም በመጥራትህ አድላቸው በኃይልህም አጽና ። በፍቅርህ ጠብቅ የዘላለም በሚሆን መንግሥትህም በክርስቶስ አንድ አድርግ ። በርሱ ያለ ክብር ጽንዕ ለአንተ ይገባል ከእርሱ ጋራ ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ አሜን ።

፻፳፰ ሲወጣ አንድ ጊዜ ከገሕሉ ላይ ይባርክ ። ከዚህም በኋላ ካህኑ ለሕዝቡ ሥጋውን ዲያቆኑም ደሙን ያቀብል ። ሲያቀብልም እንደ ቀደመው ይበል ሕዝቡም ሲቀበሉ በሥጋው ላይ አንድ ጊዜ አሜን በደሙ ላይ ሁለት ጊዜ አሜን አሜን ይበሉ ።

www.ethiopianorthodox.org

፻፳፱ ወእምድኅረ ተመጠዉ ሕዝብ ።

ይ· ካ· እግዚአብሔር ዘለዓለም ብርሃነ ሕይወት ዘወሀብከነ እግዚአ ለአግብርቲከ ጽንዐተ ወዕቅበተ በዘሀሎ ዕለታት ወለያልይ እንዘ ተዐቅብ በሰላም ። ባርክ በዘይእዜ መዋዕል ወበዘይመጽእ እምድኅር በእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ። ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ ስብሐት ወእ'ኂዝ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም አሜን።

፻፴ ወእምዝ ይ· ዲ· ንአኵቶ ለእግዚአብሔር ቅድሳቶ ነሢአነ ከመ ለሕይወተ ነፍስ ይኩነነ ፈውሰ ዘተመጠነ

፫ ንስእል ወንትመኃፀን እንዘ ንሴብሖ ለእግዚአብሔር አምላክነ ።

፻፴፩ ይ· ካ· ስብሐተ እግዚአብሔር ይነግር አፉየ ወኵሉ ዘሥጋ ይባርክ ለስሙ ቅዱስ ለዓለም ወለዓለመ ዓለም ።

ይ· ሕ· አቡነ ዘበሰማያት ኢታብአነ እግዚአ ውስተ መንሱት ።

፻፴፪ ይ·ዲ· ተመጠነ እምሥጋሁ ቅዱስ ወእምደሙ ክቡር ለክርስቶስ ።

፻፳፱ ሕዝቡም ከተቀበሉ በኋላ ።

ይ· ካ· ለዘላለሙ የሕይወት ብርሃን የምትሆን እግዚአብሔር አቤቱ ባለው መዓልትና ሌሊት ለኛ ለባሮችህ በሰላም እየጠበቅህ መጠበቅን ጽናትንም የሰጠኸን በዛሬው ዕለት ኋላም በሚመጣው ዕለት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ባርክ ። በርሱ ያለ ክብር ጽንዕ ለአንተ ይገባል ከእርሱ ጋራ ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ አሜን ።


፻፴ ከዚህ በኋላ ይ· ዲ· ሥጋውን ደሙን ተቀብለን እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን ለነፍሳችን አነዋወር መድኃኒት ይሆን ዘንድ የተቀበለን እኛ አምላካችንን እግዚአብሔርን እያመሰገን እንለምናለን አደራም እንላለን ።

፻፴፩ ይ· ካ· አንደበቴ የእግዚአብሔርን ምስጋና ይናገራል። የሥጋ ፍጥረ ትም ሁሉ ቅዱስ የሚሆን ስሙን ያመሰግናል ለዘላለሙ ።

ይ· ሕ· በሰማይ ያለህ አባታችን ሆይ አቤቱ ወደ ፈተና አታግባን ።

፻፴፪ ይ· ዲ· ከክርስቶስ ከቅዱስ ሥጋ ውና ከክቡር ደሙም ተቀበልን ።

www.ethiopianorthodox.org




በይእቲ ሌሊት እንተ ባቲ እመ ያገብእዎ ነሥአ ኅብስተ በእደዊሁ ቅዱሳት ወብፁዓት እለ እንበለ ርስሐት ወመጠወ ለአርዳኢሁ ነጊሮ አን፡፡ ይብል ። ንሥኡ ብልዑ ዝ ኅብስት ሥጋየ ውእቱ ለዘበእንቲ አክሙ ይትፌተት ለኅድገተ ኃጢአት።


www.ethiopianorthodox.org
አክሱም ማተሚያ ቤት

፻፴፫ ይ· ካ· ስብሐተ እግዚአብሔር ይነግር አፉየ ወኵሉ ዘሥጋ ይባርክ ለስሙ ቅዱስ ለዓለም ወለዓለመ ዓለም ።

ይ· ሕ· አቡነ ዘበሰማያት ኢታብአነ እግዚኦ ውስተ መንሱት ።

፻፴፬ ፪ ይ· ዲ· ወናእኵቶ ይደልወነ

፪ ከመ ንሳተፍ ምሥጢረ ክብርት ወቅድስት ።

፻፴፭ ይ· ካ· ስብሐተ እግዚአብሔር ይነግር አፉየ ወኵሉ ዘሥጋ ይባርክ ለስሙ ቅዱስ ለዓለም ወለዓለመ ዓለም ።

ይ· ሕ· አቡነ ዘበሰማያት ኢታብ አነ እግዚኦ ውስተ መንሱት ።

፻፴፮ ይ· ካ· ለእመ ኮነ ዕዝል ።

እሴብሐከ ንጉሥየ ወአምላኪየ ወእ ባርክ ለስምከ ለዓለም ወለዓለመ ዓለም ።

ይ· ሕ· አቡነ ዘበሰማያት ኢታብ አነ እግዚኦ ውስተ መንሱት ።

፻፴፯ ይ· ካ· ኵሎ አሚረ እባርከከ ወእሴብሕ ለስምከ ለዓለም ወለዓ ለመ ዓለም ።

ይ· ሕ· አቡነ ዘበሰማያት ኢታብ አነ እግዚኦ ውስተ መንሱት ።

፻፴፫ ይ· ካ· አንደበቴ የእግዚአብሔርን ምስጋና ይናገራል ። የሥጋ ፍጥረትም ሁሉ ቅዱስ የሚሆን ስሙን ያመሰግናል ለዘላለሙ ።

ይ· ሕ· በሰማይ ያለህ አባታችን ሆይ አቤቱ ወደ ፈተና አታግባን ።

፻፴፬ ይ· ዲ· ክብርት ቅድስት የምት ሆን ምሥጢርን እንቀበል ዘንድ ልናመሰግነው ይገባናል ።

፻፴፭ ይ· ካ· አንደበቴ የእግዚአብሔርን ምስጋና ይናገራል ። የሥጋ ፍጥረትም ሁሉ ቅዱስ የሚሆን ስሙን ያመሰግናል ለዘላለሙ ።

ይ· ሕ· በሰማይ ያለህ አባታችን ሆይ አቤቱ ወደ ፈተና አታግባን ።

፻፴፮ ይ· ካ· ዕዝል ቢሆን ገገርዬና አምላኬ ከፍ ከፍ አደርግሃለሁ ለስምህም ምስጋናን አቀርባለሁ ለዘላለሙ ።

ይ· ሕ· በሰማይ ያለህ አባታችን ሆይ አቤቱ ወደ ፈተና አታግባን።

፻፴፯ ይ· ካ· ቀኑን ሁሉ አመሰግንሃለሁ ለስምህም ምስጋናን አቀርባለሁ ለዘላለሙ ።

ይ· ሕ· በሰማይ ያለህ አባታችን ሆይ አቤቱ ወደ ፈተና አታግባን ።

www.ethiopianorthodox.org

፻፺፰ ይ· ካ· ስብሐት እግዚአብሔር ይነግር አፉየ ወኵሉ ዘሥጋ ይባርክ ለስሙ ቅዱስ ለዓለም ወለዓለመ ዓለም ።

ይ· ሕ· አቡነ ዘበሰማያት ኢታብአነ እግዚኦ ውስተ መንሱት ።

አኮ በኵሉ ዕዝል ዘይትበሀል አላ በበዓላተ እግዚእነ ወበበዓላተ እግዝእትነ ወበእሁድ ሰንበት ።

፻፺፱ ኅዳጌ ነፍስ ።

ይ· ካ· ወካዕበ ናስተበቍዕ ዘኵሎ ይእኅዝ እግዚአብሔር አብ ለእግዚእ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ።

፪፻ ነአኵተከ እስመ ከፈልከነ ንንሣእ ዘእምቅዱስ ምሥጢር ኢይኩን ለርስሐት ወኢ ለኵነኔ አላ ለሐድሶ ነፍስ ወሥጋ ወመንፈስ ። በ፩ዱ ወልድከ ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ ስብሐት ወእኂዝ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም አሜን ።

፪፻፩ ትእዛዝ ዘባስልዮስ ።

ወለእመ ተርፈ ሥጋ ወደም ይመጥዎሙ ካህን ለካህናት ወለዲያቆናት እምቅድመ አቍርሮ ማይ ለለ፩ዱ ፪ተ ጊዜ ከመ ይኩን ሠለሰ ምስለ እንተ ነሥኡ ቀዲሙ ። ወለ

፻፺፰ ይ· ካ· አንደበቴ የእግዚአብሔርን ምስጋና ይናገራል ። የሥጋ ፍጥረትም ሁሉ ቅዱስ የሚሆን ስሙን ያመሰግናል ለዘላለሙ ።

ይ· ሕ· በሰማይ ያለህ አባታችን ሆይ አቤቱ ወደ ፈተና አታግባን ።

በዕዝል ሁሉ የሚባል አይደለም በጌታችን በዓላት በእመቤታችንም በዓላት እሑድ እሑድ ነው እንጂ ።

፻፺፱ ኅዳጌ ነፍስ ።

ይ· ካ· ዳግመኛም ሁሉን የሚይዝ የጌታችንን የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን አባት እግዚአብሔርን እንማልዳለን ።

፪፻ ከቅዱስ ምሥጢር እንቀበል ዘንድ አድለኸናልና እናመሰግንሃለን ለኃጢአት ወይም ለፍርድ አይሁን ነፍስንና ሥጋን ደመ ነፍስን ለማደስ ይሁን እንጂ ። በአንድ በልጅህ በርሱ ያለ ክብር ጽንዕ ላንተ ይገባል ። ከርሱ ጋራ ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ አሜን ።

፪፻፩ የባስልዮስ ትእዛዝ ።

ሥጋና ደም ቢተርፍ ካህኑ ማየ መቍረሩን ከመጠጣቱ አስቀድሞ ለካህናቱና ለዲያቆናቱ ለያንዳንዳቸው ሁለት ሁለት ጊዜ ይስጣቸው ቀድሞ ከተቀበሉት ጋራ ሦስት

www.ethiopianorthodox.org

እመ በዝኀ ይንሥኡ ፫ተ ፫ተ ጊዜ ወእምደምኒ ከማሁ ከመ እስመ ኢይትዌለጥ ኀበ ከዊነ ኅብስት ወወይን ።

፻፵፪ ይ· ካ· ዝማሬ ። ወእምዝ ይበል በግዕዝ በ፪ ሃሌ ሉያ ሃሌ ሉያ ። ወበእዝል ሃሌ ሃሌ ሉያ አቡነ ዘበ ሰማያት ይትቀደስ ስምከ ሥረይ ለነ ኵሎ አበሳነ ኢታብአነ ውስተ መንሱት እግዚኦ አድኅነነ እምዕለት

፪፪ እኪት ወባልሐነ እምኵሉ መንሱት ።

፻፵፫ ወእምድኅረ ተፈጸመ አስተናጽሖ። ይ ·ካ· መልአት እግዚኦ ምሥጢርከ ቅድስት እንተ ኢትማስን ዘወሀብከነ ለነ ኃይለ ወመድኀኒተ ተዝካረ ሞትከ ዘሀልው ምስሌከ ።

፻፵፬ ወርኢነ ምሥጢረ ትንሣኤከ ቅድስት ወአውረሰነ ሕይወተ ወዕቀበነ ቦቱ በዛቲ ሰዓት ወበኵሉ ጊዜ እስመ አንተ ንጉሥ ክቡር ላዕለ ኵሉ እግዚእነ ወአምላክነ ወመድኀኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ለከ ናዐርግ አኰቴተ ዕበየ ወክብረ ምስለ አቡከ ኄር ሰማያዊ ወምስለ መንፈስከ ቅዱስ ማሕየዊ ለዓለመ ዓለም አሜን ።

፻፵፭ ጸሎት እምድኅረ ማየ መቍረር ኅቡረ ይበሉ ዘኵሎሙ ውእቱ ።

ይሆን ዘንድ የተረፈውም ብዙ ቢሆን ሦስት ሦስት ጊዜ ይቀበሉ ። ከደሙም እንደዚሁ ኅብስትና ወይን ወደመሆን አይለወጥምና ።

፻፵፪ ይ· ካ· ዝማሬውን ። ከዚህም በኋላ ይህን ይበል። በግዕዝ በ፪ ሃሌ ሉያ ሃሌ ሉያ በዕዝል ደግሞ ሃሌ ሃሌ ሉያ በሰማይ ያለህ አባታችን ሆይ ስምህ ይቀደስ ኃጢአታችንን ሁሉ አስተሥርይልን አቤቱ ወደ ፈተና አታግባን ከክፉ ቀን አድነን ከፈተናም ሁሉ አድነን።

፻፵፫ አስተናጽሖ ከፈጸመ በኋላ ። ይ· ካ· አቤቱ የማታልፍ ቅድስት ምሥጢርህ ለሁሉ ተሰጠች ። ካንተ ጋራ ያለ የሞትህን መታሰቢያ ኃይልንና መድኃኒትን ለኛ የሰጠኸን ።

፻፵፬ ክብርት የምትሆን የትንሣኤህንም ምሥጢር አየን ሕይወትንም አውርሰን ። በዚህች ሰዓት በየጊዜውም ሁሉ በርሱ ጠብቀን ። ጌታችንና አምላካችን መድኃኒታችንም ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ በሁሉ ላይ የከበርህ ንጉሥ አንተ ነህና ላንተ ምስጋናን ገናንነትን ክብርንም እና ቀርብልሃለን ። ሰማያዊ ከሚሆን ከቸር አባትህ ጋራ ማሕየዊ ከሚሆን ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ ለዘላለሙ አሜን ።

፻፵፭ ከማየ መቍረር በኋላ የሚጸለይ ጸሎት ነው የሁሉም ነውና በአንድነት ይድገሙ ።

www.ethiopianorthodox.org

እጼሊ ኀቤከ ወእስእለከ እግዚእየ ወአምላኪየ ኖላዊ ኄር ዘአፍቀርከ መርዔተከ ወመጠውከ ነፍሰከ ቤዛ አባግዒከ ከመ ተሀበኒ ሥጋከ ወደ መከ መብልዐ ጽድቅ ዘበአማን ወስቴ ሕይወት ዘለዓለም ።

፻፵፮ ወካዕበ እስእለከ ወአስተበቍዐከ አ እግዚእየ ከመ ኢይግአዝ ወኢያ ርስሕ ነፍስየ ወሥጋየ ዝንቱ ሥጋከ ወደምከ ዘነሣእኩ አላ ይኩነኒ ዘያሐይወኒ ወዘያጥዕየኒ ወዘያሌ ብወኒ ፈሪሀ ዚአከ ወዘይሜህረኒ አፍቅሮተከ ከመ አድሉ ለከ በኵሉ መዋዕለ ሕይወትየ ወእሰብሕከ ዘእንበለ አጽርዖ ።

፻፵፯ አ እግዚአ አንጽሓ ለነፍስየ ወካ ዕበ አጽርዖ ከመ ትኩን ለከ መሥ ዋዕተ ወረስዮ ለልብየ ይሕየው ወይኅድር ወይምላእ ላዕሌሁ መንፈስ ቅዱስ እስመ ሥጋከ ወደመከ ነሣእኩ በተአምኖ ወተመጠውኩ እምእደ ካህናቲከ ወበላዕኩ እስመ ለከ ስብሐት ለዓለመ ዓለም አሜን ።

፻፵፰ ይ፡ ዲ፡ በእንተ አኰቴትነ ናስተበ ቍዕ ከመ እግዚአብሔር በመጽ ሐፈ ሕይወት ይጽሐፍ ስእለተነ ወአምላክ ዘለዓለም ይዘከረነ በም ዕራፈ ቅዱሳን በዘኢአሁ ብርሃን ።

አቤቱ ጌታዬ አምላኬ ወዳንተ እጸ ልያለሁ እለምንሃለሁም መንጋህን የወደድህ ቸር ጠባቂ ለበጎችህ ቤዛ ሰውነትህን የሰጠህ በእውነት የጽ ድቅ መብል ሥጋህንና የዘለዓለም የእውነት መጠጥ የሚሆን ደምህን ትሰጠኝ ዘንድ ።

፻፵፮ ዳግመኛም ጌታዬ ሆይ ይህ የተቀበልሁት ሥጋህና ደምህ ሥጋዬንና ነፍሴን እንዳያስነቅፍና እንዳያሳድፍ እለምንሃለሁ እማል ድሃለሁ ። ፈጽሞ የሚያድነኝ አንተን መፍራትንም የሚያስረዳኝ ፍቅርህንም የሚያስተምረኝ ይሁን እንጂ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ ላንተ አደላ ዘንድ ያለ ማቋረጥም አመሰግንህ ዘንድ ።

፻፵፯ አቤቱ ሰውነቴን አንጻት ላንተ መሥዋዕት ትሆን ዘንድ ዳግመኛም አጽራት ልቡናዬንም እንዲድን መንፈስ ቅዱስ እንዲያድርበትና እንዲመላበት አድርገው ። ሥጋ ህና ደምህን አምኜ ተቀብያለሁና ከካህናቱም እጅ ተቀብዬ በላሁ ላንተ ምስጋና ይገባል ለዘላለሙ አሜን ።

፻፵፰ ይ፡ ዲ፡ ስለ ማመስገናችን እንማል ዳለን እግዚአብሔር በሕይወት መጽሐፍ ልመናችንን ይጽፍ ዘንድ ለዘላለሙ የሚኖር አምላክም በቅዱ ሳን ማደሪያ በርሱ ብርሃን ያስበን ዘንድ ።

www.ethiopianorthodox.org

፻፵፱ በእንተ እለ ተድኅሩ አበዊነ ወአኀዊነ ወአኃቲነ ናስተብቍዕ ከመ እግዚአብሔር ይጸግዎሙ ጽሒቀ ወያስተሐምም ለኵሉ ወይሚጥ እምኔሆሙ ማእሰረ ዝንቱ ዓለም ወየሀቦሙ ግዕዘ ወፍቅረ አሚነ ወተስፋ ሠናየ በእንተ ሥጋሁ ወደሙ ለወልደ እግዚአብሔር ለዓለመ ዓለም አሜን ለይኩን ለይኩን ።

፻፶ ይ· ካ· አንብሮ እድ ።

እግዚአብሔር ዘለዓለም ብርሃነ ሕይወት ዘኢይጠፍእ ነጽሮሙ ለአግብርቲከ ወለአእማቲከ ወዝራእ ውስተ ልቦሙ ፈሪሆተ ስምከ ይፍረዩ በበረከት ወኀሎልቆሙ ምስለ እለ ተውህቦሙ ሥጋከ ወደምከ ።

፻፶፩ ወይኩን እዴከ ዘየኀድር ላዕሌሆሙ ዲበ እለ አትሐቱ አርእስቲሆሙ ቅድሜከ ሕዝብከ እድ ወአንስት አእሩግ ወሕፃናት ደናግል ወመነኮሳት ዕቤራት ወእጓለ ማውታ ።

፻፶፪ ወኪያነሂ ደምር ህየ ወክድን ወርዳእ ወአጽንዕ ውኀይል በኃይለ ሊቃነ መላእክቲከ እምኵሉ ምግባረ እኩይ አግኅሠነ ወውስተ ኵሉ ምግባረ ሠናይ ደምረነ ።

፻፵፱ ወደ ኋላ ስላሉ አባቶቻችንና ወንድሞቻችን ስለ እኅቶቻችንም እንማልዳለን እግዚአብሔር ትጋትን ይሰጣቸው ዘንድ ለሁሉም ያስብ ዘንድ ። የዚህን ዓለም ማሠሪያን ከነርሱ ይመልስ ዘንድ ሥርዓትን ፍቅርንና ማመንን በጎ ተስፋንም ይሰጣቸው ዘንድ ስለ እግዚአብሐር ልጅ ሥጋና ደም ለዘላለሙ አሜን ይሁን ይሁን ።

፻፶ ይ· ካ· አንብሮ እድ ።

ለዘላለሙ የማይጠፋ የሕይወት ብርሃን እግዚአብሔር ሆይ ወንዶችንና ሴቶችን ባሮችህን ተመልከታቸው ስምህን መፍራትንም በልቡናቸው ዝራ በረከትን ያፈሩ ዘንድ ሥጋህና ደምህ ከተሰጣቸውም ጋራ ቍጠራቸው ።

፻፶፩ እጅህም በላያቸው የሚያድር ይሁን ። ራሳቸውን በፊትህ ዝቅ ዝቅ ባደረጉ በወገኖችህ ላይ በወንዶቹም በሴቶቹም በሽማግሌቹና በሕፃናቱ በደናግሉና በመነኰሳቱም በባልቴቶችና አባት እናት በሞቱባቸው ላይ ።

፻፶፪ እኛንም ከዚያ ጨምር ። ሠውርና እርዳ አጽና በመላእክት አለቆች ኀይልም አበርታ ። ከክፉ ሥራ ሁሉ ለየን በበጎውም ሥራ ሁሉ አንድ አድርገን ።

www.ethiopianorthodox.org

፻፶፫ በ፩ዱ ወልድከ ዘቦቱ ለከ ምስሌሁ ወምስለ ቅዱስ መንፈስ ስብሐት ወእኂዝ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም አሜን ።

፻፶፬ ይ· ካ· ንፍቅ ወዕቀቦሙ በርትዕት ሃይማኖት በስብሐት ወክብር በኵሉ መዋዕለ ሕይወቶሙ ።

፻፶፭ ወረስዮሙ ውስተ ፍቅር ወሰላም እንተ ትትሌዓል እምኵሉ ሕሊና ወእምኵሉ ልቡና በስእለት ወበአስተበቍዖት እንተ ትገብር በእንቲአነ እግዝእተ ኵልነ ወላዲተ አምላክ ቅድስት ወንጽሕት ማርያም ወበ፬ቱ ዓበይት ብርሃናውያን ሚካኤል ወገብርኤል ሩፋኤል ወሱርያል ወበ፬ቱ እንስሳ እለ እንበለ ሥጋ ወበ፳ወ፬ ካህናተ ሰማይ ።

፻፶፮ ወአበዊነ ልዑላነ ዝክር ቅዱሳን አብርሃም ይስሐቅ ወያዕቆብ አርእስተ አበው ወዮሐንስ መጥምቅ ፲ወ፬፼ወ፵፻ ሕፃናት ቅዱሳን ወአበዊነ ሊቃውንት ሐዋርያት ቅዱሳን ወቅዱስ ማርቆስ ሐዋርያ ወሰማዕት ወወንጌላዊ ፸ወ፪ቱ አርድዕት ፭፻ ቢጽ ፫፻፲ወ፰ቱ ርቱዓነ ሃይማኖት ፻፶ቱ ደቂቅ አናንያ ወአዛርያ ወሚሳኤል ወ፫ቱ ደቂቅ ቅዱሳን ።

፻፶፫ ባንድ ልጅህ በርሱ ያለ ክብር ጽንዕ ለአንተ ይገባል ። ከርሱ ጋራ ከመንፈስ ቅዱስም ጋራ ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ አሜን ።

፻፶፬ ይ· ካ· ንፍቅ በሕይወታቸው ዘመን ሁሉ በቀናች ሃይማኖት በጌትነትና በክብር ጠብቃቸው ።

፻፶፭ ከሕሊና ሁሉ ከልቡናም ሁሉ ከፍ ከፍ ባለች ሰላምና ፍቅር አኑራቸው ። አምላክን የወለደች የሁላችን እመቤት ቅድስት ንጽሕት ማርያም ስለኛ በምታደርገው ልመናና አማላጅነት ። ብርሃናውያን በሚሆኑ በአራቱ ታላላቆች በሚካኤልና በገብርኤል በሩፋኤልና በሱርያል ሥጋ በሌላቸው በአራቱ እንስሳም በሀያ አራቱም ካህናተ ሰማይ ።

፻፶፮ ቅዱሳን በሚሆኑ የስማቸው አጠራር ከፍ ባለው በአበው አለቆች በአብርሃምና በይስሐቅ በያዕቆብም በመጥምቁ ዮሐንስም ቅዱሳን በሚሆኑ በአሥራ አራት እልፍ ከአራት ሺህ ሕፃናት ቅዱሳን በሚሆኑ ሊቃውንት በአባቶቻችን በሐዋርያት ሐዋርያና ሰማዕት ወንጌላዊም በሚሆን በቅዱስ ማርቆስ በ፸፪ቱም አርድእት በአምስት መቶም ባልንጀሮች ሃይማኖታቸው በቀና በ፫፻፲፰ ሊቃውንት በ፻፶ቱ ደቂቅ በአናንያና በአዛርያ በሚሳኤልም ቅዱሳን በሚሆኑ በ፫ቱ ደቂቅ ።

www.ethiopianorthodox.org

፻፶፯ ወቅዱስ እስጢፋኖስ ሊቀ ዲያቆ
ናት ወቀዳሜ ሰማዕት ወቅዱስ
ጊዮርጊስ ወቅዱስ ቴዎድሮስ
ምሥራቃዊ ወቅዱስ በናድሌዎስ ።
ወቅዱስ መርቆሬዎስ ወቅዱስ
ማማስ ወቅዱስ አቦሊ ወቅዱስ
ፊላታዎስ ወቀዱስ መርምህናም
ወቅዱስ አባዲር ወቅዱስ ገላውዴ
ዎስ ወቅዱስ ፋሲላደስ ወቅዱስ
ፊቅጦር ወቅዱስ ሚናስ ወቅዱስ
ቂርቆስ ወእሙ ኢየሉጣ ወኵሎሙ
ሰማዕታት ወአባ ኖብ ድንግል አዛል
ወመስተጋድል ሰማዕተ ዋሕድ ።
ወእግዚእ አብ ዐቢይ ወጻድቅ አባ
እንጦንስ ወአቡነ አባ ጳውሊ
ወአበዊነ ቅዱሳን ፫ቱ መቃርሳት
ወአቡነ አባ ዮሐንስ ሐጺር
ወጻድቅ አባ ቡላ ወአቡነ አባ
ብሶይ ወአቡነ አባ አሞን ወአቡነ
አባ ዮሐንስ ከማ ወአቡነ አባ
ጳንጦሌዎን ወአቡነ አባ ሲኖዳ
ወአቡነ አባ ብስንዳ ወአቡነ አባ
ለትጹን ወአቡነ አባ ጳኵሚስ
ወአቡነ አባ አበከረዙን ወአቡነ
አባ በርሱማ ወአበዊነ ቅዱሳን
ሮማውያን መክሲሞስ ወደማቴዎስ
ጽኑዕ ወቅዱስ አባ ሙሴ ፵ወ፱ቱ
ሰማዕታት ወኵሎሙ ለባስያነ

፻፶፯ የዲያቆናት አለቃ የሰማዕታትም
መጀመሪያ በሚሆን በቅዱስ እስጢ
ፋኖስ በቅዱስ ጊዮርጊስም የምሥ
ራቅ ሰው በሚሆን በቅዱስ ቴዎ
ድሮስ በቅዱስ በናድሌዎስም
በቅዱስ መርቆሬዎስም በቅዱስ
ማማስ በቅዱስ አቦሊ በቅዱስ
ፊላታዎስ በቅዱስ መርምህናም
በቅዱስ አባዲርም ። በቅዱስ
ገላውዴዎስም በቅዱስ ፋሲለደስ
በቅዱስ ፊቅጦርም በቅዱስ
ሚናስም በቅዱስ ቂርቆስ በእናቱ
በኢየሉጣም በሰማዕታትም ሁሉ ።
የወልድ ዋሕድ ሰማዕት ኃያል
ተጋዳይና ድንግል በሚሆን በአባ
ኖብ ጌታና ደገኛ አባት በሚሆን
በጻድቁ በአባ እንጦንስም በአባታ
ችን በአባ ጳውሊ በቅዱሳን አባቶ
ቻችን በሦስቱ መቃርሳትም በአባ
ታችን በአባ ዮሐንስ ሐጺር
በጻድቁ በአባ ቡላም በአባታችን
በአባ ብሶይም በአባታችን በአባ
አሞንም በአባታችን በአባ ዮሐንስ
ከማ በአባታችን በአባ ጳንጠ
ሌዎንም በአባታችን በአባ ሲኖዳም
በአባታችን በአባ ብስንዳም በአባ
ታችን በአባ ለትጹንም በአባታችን
በአባ ጳኵሚስ በአባታችን በአባ
አበከረዙን በአባታችን በአባ
በርሱማ በአባቶቻችን ቅዱሳን
ሮማውያን በመክሲሞስና በደማቴ
ዎስ ጽኑ ቅዱስ በሚሆን በአባ
ሙሴም በአርባ ዘጠኙ ሰማዕታት

www.ethiopianorthodox.org

መስቀል ጻድቃን ወኄራን ወመልአከ ዛቲ ዕለት ቡርክት ።
በረከቶሙ ወጸጋ ረድኤቶሙ ወትንብልና ሣህሎሙ ወትረ የሀሉ ምስሌየ ወምስለ ኵልክሙ አሜን።

፻፶፰ ይ· ሕ· አ ንጉሠ ሰላም ሰላማዊ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰላመከ ሀበነ ወአጽንዕ ለነ ሰላመከ ወሥረይ ለነ ኃጣውኢነ ወረስየነ ድልዋነ ከመ ንሑር ወንእቱ ውስተ አብያቲነ በሰላም ።

፻፶፱ ይ· ዲ· አድንኑ አርእስቲክሙ ኀበ እግዚአብሔር አምላክነ በእደ ገብሩ ካህን ከመ ይባርክሙ ።
ይ· ሕ· አሜን እግዚአብሔር ይባርከነ ወይሣሃለነ ።

፻፷ ይ· ካ· እንዘ ይባርክ በትእምርተ መስቀል ።
አ እግዚኦ አድኅን ሕዝበከ ወባርክ ርስተከ ቡራኬ ፫ተ ጊዜ ላዕለ ሕዝብ ።
ረዐዮሙ ወአልዕሎሙ እስከ ለዓለም ወዕቀባ ለቤተ ክርስቲያንከ ቅድስት እንተ አጥረይካ ወቤዘውካ በደሙ ክቡር ለዋሕድ ወልድከ እግዚእነ ወአምላክነ ወመድኃኒነ ኢየሱስ ክርስቶስ ።

፻፷፩ ወዘጸዋዕካ ትኩን ማኅደረ ለነገሥት ወለመኳንንት ለዘመድ ንጹሕ

መስቀልን በለበሱ ደጋግ በሚሆኑ በጻድቃንም ሁሉ በተባረከች በዚህች ቀን መልአክም በረከታቸውና የረድኤታቸውም ጸጋ የይቅርታቸውም ልመና ዘወትር በኔና በናንተ ላይ ይኑር አሜን ።

፻፶፰ ይ· ሕ· የፍቅር ባለቤት የሰላም ንጉሥ ሰላማዊ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ሰላምህን ስጠን ሰላምህንም አጽናልን ። ኃጢአታችንንም ይቅር በለን በሰላም ወደ ቤታችን ሄደን እንገባ ዘንድ የበቃን አድርገን ።

፻፶፱ ይ· ዲ· ወደአምላካችን ወደእግዚአብሔር ፊት ራሳችሁን ዝቅ ዝቅ አድርጉ አገልጋዩ በሚሆን በካህኑ እጅ ይባርካችሁ ዘንድ ።
ይ· ሕ· በእውነት እግዚአብሔር ይባርከን ይቅር ይበለን ።

፻፷ ይ· ካ· በመስቀል አመሳቅሎ ሲባርክ ።
አቤቱ ሕዝብህን አድን ርስትህንም ባርክ ።
በሕዝቡ ላይ ሦስት ጊዜ ይባርክ ።
እስከ ዘላለሙ ጠብቃቸው ከፍ ከፍም አድርጋቸው በአንድ ልጅህ በጌታችንና በአምላካችን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በክቡር ደሙ የዋጀሃት ቤዛም የሆንካት ቅድስት ቤተ ክርስቲያንህንም ጠብቃት ።

፻፷፩ ለነገሥታትና ለመኳንንት ለንጹሕ ወገንና ቅዱስ ለሆነ ሕዝብ ማደሪያ

www.ethiopianorthodox.org

ወለሕዝብ ቅዱስ እለ መጻእክሙ ወእለ ተጋባእክሙ ወእለ ጸለይ ክሙ ውስተ ዛቲ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እለ በላዕክሙ ሥጋሁ ቅዱስ ወእለ ሰተይክሙ ደሞ ክቡረ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ይሥረይ ለክሙ ኃጢአተክሙ ዘገበርክሙ እመሂ በአእምሮ አው በኢያእምሮ በዘኀለፈ ይምሐር ክሙ ወበዘይመጽእ ይዕቀብክሙ በእንተ ሥጋሁ ሥጋ መለኮት ወበእንተ ደሙ ደመ ሕግ ወሥር ዓት ኢየሱስ ክርስቶስ ወልደ እግ ዚአብሔር ጸባዖት ወወልደ ማር ያም ንጽሕት በድንግልና ሕሊና ወበድንግልና ሥጋ ኅትምት ለዓ ለመ ዓለም አሜን ።

ትሆን ዘንድ የጠራሃት በዚች ቅድ ስት ቤተ ክርስቲያን መጥታችሁ ተሰብስባችሁ የጸለያችሁ የጌታች ንን የኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ሥጋውን የበላችሁ ክቡር ደሙንም የጠጣችሁ በማወቅ ወይም ባለማ ወቅ የሠራችሁትን ኃጢአታችሁን ይቅር ይበላችሁ ። ሥጋ መለኮት ስለሚባል ሥጋው የሕግና የሥር ዓት ደም ስለሚሆን ደሙ የአሸናፊ የእግዚአብሔር ልጅ በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ሕሊናም ኅትምት የምትሆን የማርያም ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ባለፈው ይቅር ይበላችሁ በሚመጣውም ይጠብቃችሁ ለዘላ ለሙ አሜን ።

፻፰፱ ወእምድኅረ ፈጸመ ግብር የሀብ ቡራኬ ወውእቱ ይባርክ በአጽባ ዕቱ ውስተ ፍጽሞሙ ለሕዝብ ። ቀሳውስትሰ በተአኀዞ እድ ይትባ ረኩ በበይናቲሆሙ ።

፻፰፱ ሥራውን ከፈጸመ በኋላ ቡራኬ ይስጥ ። እርሱም በጣቱ የሕዝቡን ፊታቸውን ይባርክ ።ቀሳውስቱ ግን እጅ በእጅ ተያይዘው እርስ በርሳቸው ይባረኩ በሚባርክበትም ጊዜ ለቄሶቹ እንዲህ ይበል ።

ወሶበ ይባርክ ይበል ለቀሳውስት ሢመተ እዴሁ ለአቡነ ጴጥሮስ ። ወለሊሆሙ ይበልዎ እግዚአብሔር ይሢምከ ውስተ ዘለዓለም መንግ ሥቱ ።

የአባታችንየጴጥሮስ የእጁ ሹመት። እነርሱም ይበሉት ። እግዚአብሔር በዘላለም መንግሥቱ ይሹምህ ።

ወለዲያቆናትሂ እግዚአብሔር ልዑል ይባርከ ወያብርህ አዕይንተ አል ባቢከ ።

ለዲያቆናቱም እንዲህ ይበል ። ልዑል እግዚአብሔር ይባርክህ ዐይነ ልቡናህንም ያብራልህ ።

ለምእመናንሂ እግዚአብሔር ልዑል ይባርከ ወያርኢ ገጾ ላዕሌከ ።

ለምዕመናንም እንዲህ ይበል ልዑል እግዚአብሔር ይባርክህ ፊቱንም

www.ethiopianorthodox.org

ወለአንስትሂ እግዚአብሔር ልዑል ይባርኪ. ወያርኢ. ገጾ ላዕሌኪ. ።

፻፴፫ ወእምዝ ይ· ካ· እግዚአብሔር የሃሉ ምስለ ኵልክሙ ።

፻፴፬ ይ· ሕ· ምስለ መንፈስከ አሜን እግዚአብሔር ይባርከነ ለአግብርቲሁ በሰላም ሥርየተ ይኩነነ ዘተመጠነ ሥጋከ ወደመከ አብሐነ በመንፈስ ንኪድ ኵሎ ኃይሎ ለጸላኢ. በረከተ እዴከ ቅድስት እንተ ምልእተ ምሕረት ኪያሃ ንሴፎ ኵልነ እምኵሉ ምግባረ እኩይ አግኅሠነ ወውስተ ኵሉ ምግባረ ሠናይ ደምረነ ።

፻፴፭ ቡሩክ ዘወሀበነ ሥጋሁ ቅዱስ ወደሞ ክቡረ ጸጋ ነሣእነ ወሕይወተ ረከብነ በኃይለ መስቀሉ ለኢየሱስ ክርስቶስ ኪያከ እግዚኦ ነአኵተከ ነሢአነ ጸጋ ዘእመንፈስ ቅዱስ ። ኢትርግፅ ርግፅ

፪ ይ· ዲ· እትዉ በሰላም ።

፻፴፮ ትእዛዝ ።

ኢይደሉ እምድኅረ ተመጥዎ ቍርባን ተሐጽቦ እእዳው ወእእጋር ወተዓርቆ አልባስ ወሰጊድ ወአስተብርኮ ወወሪቀ ምራቅ ወአውጽኦ ደም ቀሪጸ አጽፋር ወተላጽዮ ፀጕር ሐዊረ ፍኖት ወተፋትሖ ምስለ

ይግለጽልህ ። ለሴቶችም እንዲሁ ይበል ልዑል እግዚአብሔር ይባርክሽ ፊቱንም ይግለጽልሽ ።

፻፴፫ ከዚህ በኋላ ይ· ካ· እግዚአብሔር ከሁላችሁ ጋራ ይኑር ።

፻፴፬ ይ· ሕ· ከመንፈስህ ጋራ አሜን እግዚአብሔር እኛን ባሮቹን በሰላም ይባርከን ። የተቀበልነው ሥጋህና ደምህ ለሥርየት ይሁነን። የጠላትን ኀይል ሁሉ በመንፈስ እንረግጥ ዘንድ አሠልጥነን ። ምሕረትን የተመላች ክብርት የምትሆን የእጅህን በረከት ሁላችን ተስፋ እናደርጋለን ከክፉ ሥራ ሁሉ አርቀን በበጎውም ሥራ ሁሉ አንድ አድርገን ።

፻፴፭ ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙንም የሰጠን ቡሩክ ነው ። ጸጋን ተቀበልን ደኅንነትንም በኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀሉ ኀይል አገኘን። አቤቱ፡ ከመንፈስ ቅዱስ የተገኘ ጸጋን ተቀብለን አንተን እናመሰግናለን ።

ይ· ዲ· በሰላም ግቡ ።

፻፴፮ ትእዛዝ ። ቍርባን ከተቀበሉ በኋላ እጅና እግር መታጠብ ከልብስም መራቀት መስገድና መንበርከክ አይገባም ። ምራቅን መትፋትና ደም ማውጣት ጥፍርን መቍረጥ ጠጕርንም መላጨት መንገድ መሄድ ከሰውም ጋራ መፈራረድ

www.ethiopianorthodox.org

ሰብእ ወበዊእ ውስተ ቤተ ብለኔ በሊዕ ወሰትይ ዘእንበለ ዐቅም ወተራክቦ ምስለ ብእሲት ወዘ ይመስሎ ለዝንቱ ኢይደሉ እምድኅረ ነሢአ ቍርባን ።

፻፷፪ ይ· ካ· ንፍቅ እንዘ ይሜጡ አውሎግያ ፪ተ ዘተመይጡ ቅድመ እግዚአብሔር አምላክነ ወፈጣሪነ ዘይሁብ ሠናይቶ ወሲሳየ ለኵሉ ዘሥጋ አንተ ውእቱ ዘትሁብ በረከተ ለአግብርቲከ ለእለ ይፈ ርሁ ስመከ ቅዱሰ ስፋሕ የማነከ ቅዱሰ ዮምኒ በዛቲ ሰዓት ።

፻፷፫ ወባርክ ዘንተ ኅብስተ በላዕለ እዴየ ወይኩን በረከትከ ወሠናያ ቲከ በላዕሌሁ ወይኩን ዓዲ ለኵሉ ዘይነሥእ እምኔሁ መድኃኒተ ወፈ ውሰ ለነፍስ ኃይለ ወጽንዐ ለሥጋ ወለሥርየተ ኃጢአት ዘንተ ሲሳየ ዘወሀብከነ ለአኰቴተ ዚአከ ውእቱ ወከመ ንሰብሐ ለመንግሥትከ ሥሉስ ቅዱስ አብ ወወልድ ወመን ፈስ ቅዱስ ።

፻፷፬ እ እግዚእ በረከተ ዚአከ ይኩን ላዕለ ዝንቱ ኅብስት ወላዕለ ዘይሁብ ወላዕለ ዘይነሥእ እምኔሁ ወላዕለ እለ ይትለአኩ በፈሪሆትከ።

ወደ ውሽባ ቤት መግባት ያለመጠን መብላትና መጠጣት ከሴት ጋራ መገናኘት ይህን የመሰለ ሁሉ ቍርባን ከተቀበሉ በኋላ አይገባም።

፻፷፪ ይ· ካ· ንፍቅ አስቀድሞ የተመለሱ ትን ሁለቱን ኅብስቶች ሲሰጥ ። አምላካችንና ፈጣሪያችን እግዚአብ ሔር ለሥጋዊ ሁሉ ቸርነትንና ምግብን የሚሰጥ ነው ። ቅዱስ ስምህን ለሚፈሩ ባሮችህ በረከትን የምትሰጥ አንተ ነህ ዛሬም በዚህች ሰዓት ቅዱስ ቀኝህን ዘርጋ ።

፻፷፫ በእኔ እጅ ላይ ይህን ኅብስት ባርክ በረከትህና ቸርነትህ በላዩ ላይ ይሁን ዳግመኛም ከርሱ ለሚቀበል ሁሉ ለነፍስ መድኃኒትና ፈውስ ለሥጋም ኀይልና ጽንዕ ለኃጢአ ትም ማስተሥሪያ ይሁን ። ይህን ኅብስት የሰጠኸን አንተን ለማመስ ገን ነው ። ልዩ ሦስት አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ሆይ መንግሥትህ ንም እናመሰግን ዘንድ ነው ።

፻፷፬ አቤቱ ያንተ በረከት በዚህ ኅብስት ላይ በሚያቀብለውም ላይ ከርሱ በሚቀበለውም ላይ አንተን በመፍ ራት በሚያገለግሉም ላይ ይሁን ።

www.ethiopianorthodox.org

፻፸ ስብሐት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ይእዜኒ ወዘልፈኒ ወለዓለመ ዓለም አሜን ።

ተፈጸመ ሥርዓተ ቅዳሴ ዘሐዋርያት በሰላመ እግዚአ· አሜን ።

፻፸ ለአብና ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስም ምስጋና ይገባቸዋል ። ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ አሜን ።

ሐዋርያት የተናገሩት የቅዳሴ ሥርዓት ደረሰ ተፈጸመ ። በእግዚአብሔር ሰላም አሜን ።

www.ethiopianorthodox.org